


ተድላ ወርቁ በድሬዳዋ አካባቢ በደርግ ነፈሰገዳዮች በ1970 ዎቹ ከተገደሉት የኢሕኣፓ ከዋክብት አንዱ ነበር

# ኢትዮጵያ


የካቲት/መጋቢት 3ኛ ዓመት



**ርእስ አንቀጽ ገፅ 2**
ኢትዮጵያ ከተባበረ ሕዝብ ትግል ወዲያ መድኅን የላትም

//

**ገፅ 3**

**ዜና ከተባለ**

**ምን ይሰማ....... አገር**

//

**ዜናዎች ገፅ 4**

//

**ትናንትና ገፅ 5**
በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤የጓድ ቆንጂት ተክሉ ክራሞት

//

**ነጻ ሀሳብ ገፅ 6**
ዓለምና ዘመን ፊታቸውን ያዞሩባት ሀገር !


## አጫጭር ዜናዎች

- ኢጋድ የተባለው የምስራቅና አፍሪካና የአፍሪካ ቀንድ ስብስብ የሆነው ተቋም ስር የሚሰራው ሳገን የተባለው መቀመጫው ናይሮቢ ኪንያ የሆነው አካል እንዳቀረበው መረጃ ከሆነ የኢርትራ ዜጎችና ባላስልጣኖች ስደተኛውን በማጓጓዝና በመሸጥ ዋና ጠያቂዎች ናቸው ብሏል ። እነዚህም ከወያኔዎች ፤ ከሱዳን ዜጎች ጋር በመተባባር ስደተኞችን ወደ ሊቢያና አውሮጳ እንደሚሰዱም መረጃዎችም አሉን ሲሉ ከሰዋል ። የአውሮጳ ኤምባሲዎችም በአዲስ አበባ ሆነ ካርቱም ቪዛ እንደሚሸጡ የታወቀ ሲሆን ወያኔ በበኩሉ ወደ መካከለኛው ምስራቅና ወደ ኬንያ-- ደቡብ አፍሪቃ የሰው ሽያጩን በቁጥጥሩ ካስገባ ዓመታት አልፈዋል ሲሉ ታዛቢዎች ተችተዋል ። ጥናቱን የጠየቁት ወያኔና ሱዳን ቢሆኑም የእነሱም ሀላፊነት ሳይጠቀስ አልቀረም ።

- ተገኝ ጌታሁን ከፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰናበተ። ይህ በመለስ ዜናዊ ከስድስት ዓመት በፊት ተሹሞ የነበር ግለሰብ ከቦታው የጤና ምክንያት ጠቅሶ ስንብት ቢጠይቅም ችግሩ ፖለቲካዊና ከዛሬዎቹ ገዢዎች አለመስማማቱ መሆኑ ተጠቅሷል ። በተገኝ ፈንታ ወያኔ የሆነ ወይም ደጋፊ የሆነ ሀላፊ ይሾም ይሆናልም ተብሏል ። ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ወጣም ወረደ ምንም ስልጣን ስለሌለው ማን ተሾመ ማን ዋጋ የለውም ያሉ ታዛቢዎች የፍትህን ተቋም ወያኔ ካደቀቀው 25 አመት ሆኖታል ብለዋል ።

- ባለፈው ሰሞን የትግራዩ ፕሬዚዳንት አባይ ወልዱ ስሙን መጥራት የማይፈልገውን ኢሕአፓን አንስቶ የወልቃይት ችግር በኢሕአፓ የተቀሰቀሰ ነው ሲል ተደምጧል ። የወልቃይት ሕዝብ በደልና ግፍ ብቻ ሳይሆን ማነታችንን መቀማቱ ያብቃ ብሎ የተነሳው ወያኔን ተቃውሞ መሆኑ እየታወቀ ይህን እምቢታ ወደ ኢሕአፓ ለመላከክ መጣሩ የሚያዋጣ አይደለም ። ወያኔ በዚህም በዚያም ተወጥሯልና መውጫው መንገዱ ክስ ሳይሆን ዘረኛ አገዛዙ ማብቃት ያለበት መሆኑን ቢረዳ ያዋጣዋል ሲሉ ታዛቢዎች አስተያየታቸውን ይሰጣሉ ። ወደ አዲስ አበባ ሄደው የነበሩትን የወልቃይት ተወካዮችንም ኢዲኅና ኢሕአፓ ብሎ ወንጅሎ ማባረሩም የተገለጸ ሲሆን ይህ ድርጊት ለወያኔ የሚበጀው አለመሆኑን በቅርቡ የሚማረው ይሆናል ።

- ባለፈው ዓርብ በአዲስ አበባው አንዋር መስጊድ የተገኙ ሙስሊሞች መሪዎቻችን ይፈቱ፤ በደሉና አፈናው ያብቃ እያሉ በመጮህ ተቃውሞአቸውን አሰምተዋል ። ከተቃውሞ ቀጣይነት አንጻር ሙስሊም ዜጎች አራያ ሆነዋል ቢባል ትክክል ነው ያሉ ታዛቢዎች በአንጻሩ የሰልፍ ፈቃድ[የስብሰባ ፈቃድ ተከለከልን ብሎ ነጋ ጠባ የሚያላዝነው መድረክ ራሱን ለትዝብት አጋልጧል ሲሉ ተችተዋል ።

- ከሚዛን ወደ ቴፒ ሃምሳ ስድስት ሰዎችን አሳፍሮ ይጓዝ የነበረው የቴፒ ዩኒቨርስቲ ሰርቪስ መኪና ድልድይ ውስጥ ገብቶ የአስራ አምስት ሰዎች ህይወት ወዲያወኑ ያለፈ ሲሆን 30 የሚሆኑ ከባድ በሆነ ሁኔታ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። ጉዳት የደረሰባቸው ወገኖች ለህክምና ወደ ሀዋሳ ሲወሰዱ የተቀሩት አስር ሰዎች መኪናው የተጫናቸውና በውሃ የተወሰዱ መሆናቸውን ዘገባው አመልክቷል። በሰርቪሱ ውስጥ የነበሩት ሚኞችና ተጎጂዎች አብዛኞቹ የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ ማኅበረሰብ አባላት ናቸው።

- የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) አመራር አባል አቶ ሀብታሙ አያሌውና መምህር አብረሃም ሰለሞን፣ ማክሰኞ የካቲት 8 ቀን 2008 ዓ.ም. ከእስር የተፈቱ መሆናቸው ታውቋል፡፡ የካቲት 3 ቀን 2008 ዓ.ም.የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቶ ሀብታሙ አያሌው፣ አቶ ዳንኤል ሺበሺ፣ አቶ አብረሃ ደስታ፣ አቶ የሺዋስ አሰፋና መምህር አብረሃም ሰለሞን ከእስር እንዲፈቱ ፍርድ ቤቱ መወሰኑና የመፍቻው ትዕዛዝ ለማረሚያ ቤት አስተዳደር መድረሱ የተረጋገጠ ቢሆንም፣ ከእስረኞቹ መካከል ሁለቱ ሲፈቱ ሌሎች እስካሁን ያልተፈቱ መሆናቸው ታውቋል። በተያያዘ ዜና የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግሬስ ምክትል ኃላፊ አቶ በቀለ ገርባ እና ከሳቸው ጋር የተያዙት የፓርቲው አባላት፤ እንዲሁም የነገረ ኢትዮዮጵያ ዋና አዘጋጅ አቶ ጌታቸው ሽፈራውና የሰማያዊ ፓርቲ አባል አቶ ዳንዔል ተስፋየ አርብ የካቲት 11 ቀን 2008 ዓም ፍርድ ቤት ቀርበው አቃቤ ህጉ ምርመራዬን አልጨረስኩም በማለቱ የ28 ቀን ተጨማሪ ጊዜ የተፈቀደለት መሆኑ ተዘግቧል።

- ቃና ቴሌቪዥንን በሚል ስራ ሊጀምር ነው የተባለው ጣቢያ የወያኔ ነው ሲሉ ውስጠ አዋቂዎች አጋለጡ ። ይህ ከዱባይ ሞቢ ቡድን ጋር በሽርክነት ተቋቀመ የተባለው ጣቢያ ሀላፊ ዘረሰናይ ብርሃኔ መሃሪና፤ናዝራዊ ገብረስላሴና አዲስ ዓለማየሁ መሆናቸውም ተገልጿል ። ወያኔ በዚህም በዚያም የራሱን ጣቢያዎችና ራዲዮኖች 'እንዲሁም ድረገጾች እያሰማራ ሲሆን ሊሎች ላይ ግን ጥብቅ ቁጥጥርና እገዳ ማድረገን እየቀጠለ ነው ። የተቋሞቹ ድረገጾች ተጠለፉ ብሎ የአዞ እንባ እየረጨው ያለው አዲስ የመገናኛ ብዙሃን መቆጣጠሪያ ህግም ሊያወጣ መሆኑን ገልጿል።

- የግብፅ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ የራሳቸውን የኢንዱስትሪ ፓርክ ገንብተው ማምረት የሚችሉባቸውን ፋብሪካዎች ለመትከል፣ 120 ሚሊዮን ዶላር መመደባቸውን የግብፅ ኤምባሲ ያስታወቀ መሆኑ ወያኔ ራሱ በይፋ መግለጫ ሰጥቷል ። ከስትራተጂ አንጻር ቁልፍ በሆነችው ባሕር ዳር ከተማ ግብጾች ፈቃድ አግኝተው ግንባታ መያዛቸው ከዚህ በፊት ተዘግቧል ያሉ ክፍሎች ግብጽ ያላትን መሰረታዊ ተቃውሞና ወታደራዊ ዝግጅት በተመለከተ ምንም የአቅዋም ለውጥ ሳታደርግ ወያኔ መንበርከከ መቀጠሉ ሀገርን መጉዳቱ አይቀሬ ነውብለዋል ። ግብጾቹ ዱከምን ቢመርጡም ወያኔ መቀሌ መሆን አለበትብሎ መከራከሩን ለማወቅ ተችሏል ። ትልልቅ የግብፅ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ዞን ለማቋቋም የ200 ሔክታር መሬት ጥያቄ ለወያኔ አቅርበዋል፡፡

- የኦማር ገሌህ አምባገነናዊ አገዛዝ በጁቡቲ ሕዝብ ላይ የአፈና ተግባሩን የቀጠለ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ጋዜጠኞች ላይ ያተኮረ ጥቃት እያደረሰ መሆን ተጋልጧል ። አማር ገሌህ የሀገሩን መሬት ለፈረንሳይ፤ለአሜሪካ፤ለቻይና፤ጃፓንና ጀርመን ሰጥቶ የነዚህ ሀይሎች ድጋፍ ቢኖረውም ሕዝቡ በስፋት እየተቃወመው ስላለ እንደገና ለመመረጥ የሚያደርገው ጥረት ላይሳካ ይችላል ብለው የሚገምቱ ብዙ ናቸው ። ከዚህ ጋር በተያያዘ የኦማር ገለህ አገዛዝ ጋዜጠኛ መሀመድ ኢብራሂምን ዌይንን ይዞ ስየል እየፈጸመበት መሆኑ ተጋልጦ ተወግዟል ።


**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**





የኢትዮጵያ ጋዜጣን በተለያዩ ድረ ገጾች

EPRP.COM
ASSIMBA.ORG
DEBTERAW.COM
ወዘተ.

- FACE BOOK (ethiopianewspaper)

# ኢትዮጵያ

በኢሕአፓ የዲሲና አካባቢዉ ደጋፊ አካል
የሚዘጋጅ ወራዊ ጋዜጣ
5309 Georgia Ave. NW 2nd floor Washington DC. 20011
ስ/ቁ፡ 202 291 4217
ኢሜል፡ dc..region.eprp@gmail.com

## ርዕሰ አንቀጽ

የራቀ ይመለስ!

### ኢትዮጵያ ከተባበረ ሕዝብ ትግል ወዲያ መድኅን የላትም !!

ተደጋግሞ እንደተባለዉ የሕዝብ ጉልበቱ - ሕብረቱ ነዉ ። በአንድ ያበረ ሕዝብ ለመብቱም ሆነ ለነጻነቱ በሚያደርገዉ ትግል በቀላሉ ድልን ይቀዳጃል። የዚያኑ ያህል፤ ተነጣጥሎ ከተገኘ ደግሞ ሳይወድ በግድ የጠላቶቹ መጫወቻ መሆኑ አይቀሬ ነዉ። ይህን በሚገባ የተገነዘበዉ የወያኔ አገዛዝ በተገኘዉ የድክመት ቀዳዳ ሁሉ እየሾለከ መሠሪ ስልቶቹን በመተግበር እጅግ የሚያስፈራዉን ህብረታችንን ሲሰነጣጥር ቆይቷል ። እንዲያዉም ፤ወያኔያዊዉ አገዛዝ፤ የጸረ ሕዝብነቱንና የጸረ ኢትዮጵያነቱን ያህል፤ በአፍጢሙ ሳይደፋ እስከዛሬ ድረስ ከሥልጣን ተቆናጥጦ የመቆየቱ ምስጢር ሌላ አይደለም። ተረጋጮቹን ተገዢዎች በኃይማኖት ፤ በቋንቋና በባህል ከፋፍሎ ርስ በርሳቸዉ በጥርጣሬ እንዲተያዩና እንዳይቀራረቡ በሰይጣናዊ ትጋት ሳይታክት መሥራቱ ነዉ ። በዚህም እስከ ዛሬ በርካታ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎችን ቀጭቷል። ቁጥር ያላቸዉን ሀገራዊ የዐመጽ ጅምሮችን ከተቀሰቀሱበት ክልል ሳይሻገሩ በእንጭጩ ጨፍልቋቸዋል ።

በቅርቡ፤ አዲስ አበባን በማልማት ስም በሺህዎች የሚቆጠሩ አርሶ አደሮች በተፈናቀሉበት ዐይን ያወጣ ወያኔያዊ ዘረፋ መነሾ በኦሮሚያ ክልል የተቀጣጠለዉ ሕዝባዊ የአልገዛም ባይነት ቁጣ ይህን መሰሉ ዕጣ ከደረሳቸዉ እንቅስቃሴዎች በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚገባዉ ነዉ ። በክልሉ በሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዉስጥ በሚማሩ ተማሪዎች የተጀመረዉንና ወደተቀረዉ ኅብረተሰብ በፍጥነት የተዛመተዉን ይህንን ድንገተኛ የተቃዉሞ ማዕበል ለመግታት ዘረኛዉ አገዛዝ ልዩ ገዳይ ኃይሎቹን በማሰማራት ዘግናኝ የግፍ ርምጃዎችን ወስዷል ። አያሌ ኢትዮጵያዉያን ወገኖቻችንን በጭካኔ ገድሏል ፤ አቁስሏል ፤ ወደ እስር ቤቶችም ወርዉሯል ። ተፈጥሮአዊ ባህሪዉ ነዉና፤ ለወደፊቱም በርካታ ዜጎቻችን በአሸባሪነት ወይም ፤ ራሱ ወያኔ ቀድሞ እንዳልሰየጠነበት፤ በጠባብነት ተፈርጀዉ እንደሚሳደዱና በስዉር እንደሚገደሉ የሚጠበቅ ነዉ።

ርግጥ ነዉ ፤ወያኔ በግፈኛ አገዛዙ ዳፋ የተጫረበትን እሳት፤ ቋያ ሰደድ ሆኖ አመድ ሳያደርገዉ በፊት ለጊዜዉ ሊከላዉ ችሏል ፤ ሙሉ በሙሉ ባያጠፋዉም እንኳ። ሆኖም ሕዝባችን የአገዛዙን መሰሪነት በመገንዘብ ፤ አንዱን ብሔረሰብን በሌላዉ ላይ ለማስነሳትና የትግሉን አቅጣጫ ለማስለወጥ በሠርጎ ገብ ካድሬዎቹ አማካይነት ያደረገዉን ጥረት በማጨናገፍ ብስለቱንና አርቆ አሳቢነቱን ማስመስከሩ በራሱ የአምባገነናዊዉ ዘረኛ ሥርዓት ማክተሚያ ሩቅ አለመሆኑን የሚያመላክት ትልቅ እመርታ ነዉ። የሥርዓቱ ዕድሜና ዘለቄታ በኢትዮጵያ ሕዝብ ክፍፍል ላይ መሆኑ እየታወቀ ፤ ግጭቶች ከተፈጠሩ በኋላ የአንድነት ጠበቃ መስሎ የመቅረብ እስስታዊ ባህሪዉ ብዙዎችን ደጋግሞ ማሳሳቱን አንዘነጋዉም።

ብዙዎች ኢትዮጵያዉያን በለጋ ዕድሜያቸዉ የወደቁበት ይህ ሰፊ መሠረት ያለዉ ሕዝባዊ የአልገዛም- አሻፈረኝ ባይነት በዘረኞቹ አገዛዝ ተንገፍግፎ ለተነሳዉ ሕዝብና ለሀገር አንዳች ግልግል ከማስገኘት ይልቅ የከፋ እመቃና ጭቆና የሚያስከትል ሆኖ መደምደሙ ያሳዝናል ። መነሾ ያደረጋቸዉ ወያኔያዊ የመሬት ዘረፋና ተያያዥ ጉዳዮችም ሆኑ ሌሎቹ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ጥያቄዎች በመላይቱ ኢትዮጵያ የሚዘወተሩና በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አዕምሮ የሚመላለሱ ሆነዉ ሳለ ዐመጹ ሀገራዊ ስፋት ሳይይዝ ብቻዉን ለጨካኙ የገዢዎች ጥቃት እንዲጋለጥ ሆኗል። ለዚህ ሰበብ የሆኑ በርካታ ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉም እንደ ሕዝብ ለሚወርድብን መከራና ለተነጠቅነዉ መብት ምክንያት በሆነዉ አገዛዝ ላይ በጋራ ለመቆምና ለመታገል አለመቻላችን በዐቢይነት ሊጠቀስ የሚገባዉ ነዉ። ለዚህ ደግሞ፤ ወያኔ በሕዝቡ መሀል ያሰማራቸዉ ቅጥረኞችና ከዉድቀታቸዉ የማይማሩ ጥራዝ ነጠቆች ከሩቅ ሆነዉ ዐመጹን ከጽንፈኛ አቋማቸዉ በስተኋላ ለማሰለፍ ሌትና ቀን የነሰነሱት መርዝ በተቀረዉ ሕዝብ ዘንድ ባጫረዉ ጥርጣሬ፤ ትግሉን ከመሀልም ሆነ ከዳር ተገቢዉን ሕዝባዊ ድጋፍ አሳጥቶታል ። ለዐመጹ መዳፈንም ሆነ በትግሉ በወያኔ ለተቀጠፈዉ ሕይወትና ለደረሰዉ ጉዳት፤ እነዚሁ እኩያን የወያኔዉን አገዛዝ ያህል ተጠያቂዎች ናቸው።

እንደ አንዲት አገር ሕዝብ፤ ኢትዮጵያዉያን ሞታችንም ሆነ ሽረታችን በአንድ ላይ ነዉ። ምዕተ ዓመታትን የደረመሰዉ ታሪካችን የተጻፈዉ በጋራ የደማችን ቀለም ነዉ። ባህር አቋርጠዉ ከመጡ ወራሪዎች አስጥሎ በነጻነት ያዘለቀንም ያ ነዉ ።

ሕዝባዊዉ ዴሞክራሲያዊ ትግል ያቸንፋል!
በነጻነቷ ኮርታ፤ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር !!

## ሆኜ በሆነማ !

ከመላኩ ይስማው

የህንዶች ሃይማኖት፣ ሃቅ ሆኖ ቢሰራ፣
ዳግመኛ ሰው ብሆን፣ በዳግም ፈጠራ፣
አፈናን እምቢ እሚል፣ ፍፁም እማይፈራ!
ለህዝባዊ ትግል፣ ነዶ የሚያበራ፣
በጨለማው ሌሊት፣ መንገድ የሚመራ፣
ነበር በሆንኩ ሃይሉን፣ እሳተ-ገሞራ!
አለመሆኔ እንጂ፣ ሆኜ በሆነማ፣
የታፈነ ህዝብ ድምጽ፣ እሮሮ እንዲሰማ፣
ልክ እንደ ገሞራው፣
ልክ እንደ ደብተራው፣
ልክ እንደ ዓሊ ሁሴን፣ እንደ ሃማ ቱማ፣
እሚገት ነበረ፣ በጥበብ አውድማ!

ሰበብ ሳላበዛ፣ ምንም ሳላቅማማ !
ብሆንማ ኖሮ፣ ጀግና እንደዚያ ትውልድ፣
ብር፣ ነፍጥ ለያዘ፣ ተንጳርጵሮ እማይሰግድ፣
የጠላቱን ፊት ሲያይ፣ በፍራት የማይርድ፣
ሌቱ ያረጠ ዕለት፣ የማይርበደበድ፣
ጠዋት የገባውን፣ ቃል ማታ የማይክድ፣
ብሆንማ ኖሮ፣ ልክ እንደዚያ ትውልድ፣ የፍርሃት ማርከሻ፣
መች ያረክሳት ነበር፣ የሀገሬን ምድር፣ ያውሮፓ፣ አሜሪካ፣
ያረቡ፣ የህንዱ፣ የነቻይና ውሻ፣
ቢሆንማ ኖሮ፣ ልክ እንደ ገሞራው፣ የመጣፍ ክሂሌ፣
ቢሆንማ እንደ እሱ፣ የህዝብ ጠበቃ፣ ብዕሬ መንጎሌ፣
መች ዝም ብዬ አይ ነበር፣ ውሸቱን ሲጠርቅ፣
የምዕራብ አገልጋይ፣

የነቻይና ሎሌ !

የአረቡ፣ የህንዱ፣ የ'ንግሊዝ አለሌ !

እሞግተው ነበር፣ ብዬ አሌ ! ውሸት ነው !
ተቦክቶ ሮም፣ ለንደን፣ ሱዳን የተሠራው፣
የፈጠራ ወግህ፣ ከመቶ እማያልፈው፣

ካንተው ጋር የሚሞት፣ ፍሬ አልባ ድኩም ነው !

ኢትዮጵያዊነት ግን፣ ዘመን የማይሽረው !

እለው ነበር አዎ ! ዋልታና ማገሩ፣

ኖሮ ያለፈበት የደብተራው ክሩ !

የዮናስ፣ ተስፋዬ፣ የገሞራው ክሩ !
ህይወት ማዋለጃ፣ መፃፊያ ብዕሩ፣
ህዝባዊነት ነው፣ መሠረተ ሥሩ፣

ሲጨንቃ የማይላላ፣ የቃል ኪዳን ቁጥሩ !

ሲቆይ የሚደምቀው፣ ቀለም ምስክሩ !
የሲ አይ ኤ ጋሪ፣ የሞሳድ መጋዣ፣ የኤም አይ በቅሎ፣
አስረሽ ምችው ሲል፣ ባገር ተደላድሎ፣
የዓለም ባንክና የባዕዳን ቅምጥ፣
ወገን ላይ ተጭኖ፣ እንደዚህ ሲያናጥጥ፣
አዎ! ቢሆንማ ኖሮ፣ የነአጅሬን ብዕር፣
የቅጥረኛን ተንኮል፣ ሠንዝሮ እሚመትር፣
መች ያስችለው ነበር፣ ብዕሬ ለማየት፣ ይህን ግፍ ዝም ብሎ፣
ነበር ይዋጋ እንጅ፣ ባገሬ ምድር ላይ የሰባውን ሀሰት ገምሶ

ገምሶ ጥሎ !
አይደለም እል ነበር፣ የዚያ ትውልድ ግቡ፣
የተሰዋለት ህልም፣ የእምነት ክር ማተቡ፣
ዶክተር ፕሮፌሰር፣ የሚል ማዕረግ ለቅሞ፣
የመጣውን ገዥ፣ ተለማምጦ፣ አስታሞ፣

ጊዜ አይቶ እሚነፋ፣ ክብር ተሸክሞ !

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ዜና ከተባለ

**መሰተዋት ከድሬ**

በማፈሪያው ለመጀመር ፤

አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት ቅዱስ መጽሃፍ አጠበች ብለዋል ጥንታውያን ። እጅግም ብልጠት ያደርሳል ከሞት፤ እጅግም ስለት ይቀዳል አፎትም ተብሏል ። ሀገራችን ብዙ ዓይነት ፍጥረቶችን ወልዳለችና በሜዳ ሩጫ ባለድል ሆኛለሁና በፖለቲካውም ላስተምራችሁ የሚል ለከት ያጣ መሀይም መጥቶብናል ። መጤ ሀብታም እንዲሉ ከበርኩ አለና አንድ ሰሞን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰነፍ መሆኑን አበሰረን ። ፕሬዚዳንታችሁ ልሆንም ብቁ ነኝ ሲል ምን ይሰማ ጀሮ ብለን አለፍነው ። ቅንጅቶችን ከ1997 ኡ ምርጫ በኋላ ወያኔን ተቀበሉ ብሎም መካሪ ሆነ ። እንኳን ካዝናውን ማናምኑንም የሚዘጋ ገብጋባ ነው ይባላል ። ይህ ሁሉ የራሱ ጉዳይ ተብሎ ሊታለፍ ይችላል ። መለስ ዜናዊን መደገፉ ግን ከሀዲ የሚያሰኘው ሆኖ ሳለ በቅርቡ ደሞ የዚህን ጥራዝ ነጠቅ ሟች ቲዎሪ አቀንቃኝነት ወርሻለሁ በሚል ዕብሪት ለኢትዮጵያም ሆነ ለአፍሪካ ጠንካራ መሪ እንጂ ዴሞክራሲማ ቅንጦት ነው ሲል ለፈፈ ። የወያኔን ወንጀል ሲያወግዝም አልተሰማም መቸም። ባለውለታውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ናቀ፤ በገንዘብ ተዘባኖ ዘለፈም። የሚስማማውን ቅጽል ብናውቀውም ስሙን ኃይሌ ገብረሥላሴ ይላል ብለን እንለፈው።

አንባብያን እንኳን ለየካቲት 66 42ኛ ዓመት አደረሳችሁ ።

ዜና ከተባለ ስንል ደምቆና ጎልቶ ያለው የተካሄደውና አሁንም ተግ ተግ የሚለው የሕዝብ አመጽ ነው ። በረድ ቢልም አልጠፋም ። ወያኔ ግን አፈናውን አባባሰ እንጂ አላቆመም ። ከ 200 በላይ ገድሎ ብዙ ዎችን አቁስሎ በርካታዎችን ለእስርና ለስየል ዳርጓል ። ህጻናትም ሳይቀሩ ተገድለዋል በአርመኔው ወያኔ። ወያኔ ላይ የሕዝብ ተቃውሞ ጥንክሮ በመምጣቱና ወያኔም በመደናገጡ መርበትበት ሰፍኗልና ተጨማሪ የፈሪ ዱል መጠበቁ ተገቢ ነው ። የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን በሚል ወያኔ ወደ አምቦ ሊስፋፋ የሞከረው ለተቃውሞው ክብሪት ሆኗል ። ከአምቦ እስከ አዋሳ ሐረር ወዘተ የተዛመተው ይህ የሕዝብ ተቃውሞ በሱ ምክንያት ቢነሳም የዓመታት መብት ረገጣና ጭቆና የቀሰቀሰው ለመሆኑ ጥርጥር የለውም ። ኦሮሞ ወጣቶች በዚህ በኩል ለኳሽና መስዋዕት ከፋይም ሆነው ተመዝግበዋል ። በአዋሳም ተቃውሞ ነበር።በጋምቤላም ትጥቅ ያነገተ ትግል ተከስቷል ። በጎንደርም የወያኔን የመሬት ንጥቂያ በመቃወምና በተለይም ሕዝቡ ማንነቱን መነጠቁን በማውገዝ ብረት አዘል ትግሉን ማጧጧፍ ጀምሯል ። ድርጅት ነን በሚል በዚሁ አካባቢ ተንቀሳቀስን ስለሚሉት ግን አሳማኝ መረጃ እስካሁን አለመገኘቱን ታዛቢዎች ያቀርባሉ ።

የሕዝቡ ትግል እንደተፋፋመ ግን ይህን የየቦታውን ትግል እንዲቀናጅና እንዲደጋገፍ በማድረገ ፈንታ ከፋፋዮች ከየስርቻቸው ብቅ ብቅ ውር ውር ማለቱን ተያያዙት ። የቡርቃው ማፈሪያ ከመሸገበት አስመራ ማወናበዱን ተያያዘው ። ጎራዴያችን በአማራ ደም ይቅላ ባዩና ጌቶቹ ከወደ ላንግሌ ቨርጂኒያ ያሉት ሳይሆኑ አይቀሩም የሚባልለትም መድረክ አጣበበ። ትግሉን በክልል ደረጃ ብቻ ሊገልጹትና አጣበውም ሰለባ ሊያደርጉት ሲነሱ ሁሉም በጊዜው ተረዳ ማለትም ይከብዳል። የትግል አንድነትና ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ያሉ ያው በትምክህተኛነት ተወረፉ። “ከኢትዮጵያውያን ጋር እኛ ኦሮሞዎች ያለን ንክኪ በአዳም ልጅነታችን ብቻ ነው” ያለውና የበደኖን ጭፍጨፋ አበረታቷል በሚል የሚከሰሰው ግለሰብም አቅዋሜን አሻሽያለሁ፤ ነጻ ኦሮሚያ የሚለው የተሳሰተ አቅዋም ነው አለ ከተባለ ወዲህ ወደበፊቱ ቅዠቱ ተመልሶ ወያኔን በሚለማመጥ ደብዳቤ አማካኝነት ዋናው ጉዳይ አዲስ አበባን የኦሮሞ ግዛት እንዲባልልን ነው በማለት ራሱን አጋለጠ። አዲስ አበባ የኦሮሞም፤የአማራም፤የትግሬም የጉራጌም ፤የሃዲያና ቤኒ ሻንጉሉም ወዘተ ማለትም የሁሉም ኢትዮጵያዊ መሆኗን ስቶ ማለት ነው ። የካቲት 66ንም ሊያሳንስ የሞከረው ይህ ግሰሰብ የየካቲት ድምቀቱ የሕዝብ ህብረትና አንድነት፤ኢትዮጵያዊነት መሆኑን ዳግም መዘንጋቱንም አጋልጧል ።

ህብረት ያስፈልጋል ሲባልም ያው የዶሮ ገለባን ሚዛን የማይደፋት የዚሁ ጥረት ዕምብርት ማዕከል እንሁን ብለውም ብቅ ብለዋል--ሰሚ ቢገኝ ። ሳይውል ሳይድርም አንዳንዶቹ በመድረክ ብቅ ብለው እኛ በሰላም ሀገር ገብተን ነው ትግል የምንፈልገው ሲሉ ተናዘዋል ። ይህ በዚህ እንዳለ ግን የለየላቸው የደርግና የቀይ ሽብር ወንጀለኞች ደግሞ መድረክ ይዘው ራሳቸውንም ሻዕቢያንም ሊያሻሽጡ ሞክረውብናል ። በወያኔ በኩል አንጃዎችና ደርጎች የሚከትቡትን ጻረ ኢሕአፓ መጽሃፍት በህገር አቀፍ ደረጃ እያሰራጨና ለጸሃፊ ተብዬዎችም መድረክ እያዘጋጀ በድርጅቱ ላይ ጥቃቱን ቀጥሏል ።

ከዓመቱ ጻረ ኢሕ አፓ ኮታ መጽሃፍት አራተኛውም ሰሞኑን የያኔዎቹን መጀመሪያ አንጃዎቹን እያዳነቀ ታትሞ ለገበያ ቀርቧል ። ድርጅቱ የለም በሉ የተባለውን ግን ስቶ የትግራይ ገዢ አባይ ወልዱ በወልቃይትና በጎንደር ላለው የወያኔ ችግር ኢሕ አፓን በቀጥታ መክሰሱ አነጋጋሪ ሆኖ ይገኛል ። ወያኔን መጋፋቱና በድፍረት ወግድ ማለቱ እየጨመረ ስለመጣም የወልቃይት ጠገዴ ሆነ የጸለምት ሕዝብ ማንነቱን እያስረገጠና ወያኔን ወግድ እያለ ነው ። በሌላ በኩል የተከሰተውን የሕዝብ ተቃውሞ ለማሽመድመድ ባዕዳንም ደፋ ቀና እያሉ ናቸው ።

አሜሪካ ከድሮ ጀምሮ በኢትዮጵያ የሚደረግ ለውጥ እንደምትቃወም እንደ ዛሬ ግልጽ አድርጋ አታውቅም ቢባል ተገቢ ነው። የሰሞኑንና ያለውን ተቃውሞ ከልላ ልትገድበውና ኢትዮጵያዊነትን ልታሳጣው በራዲዮም በሌላም መስክ ሁሉ እየጣረች ነው። በኢትዮጵያ ላይ ተንኮል በመሸረብ ላይ መሆኗንም ማንም መሳት የለበትም ። ከግብጽና አረቦች ሰፈር፤ ከአሜሪካና እንግሊዝ ጎራ፤ ወያኔ ራሱ ትግልን ለማክሸፍና ሕዝብን ከፋፍሎ ለማናከስ ከሚያደርገው ጥረት ነቅቶ መጠበቅና ሊደረግ የሚገባውን ሁሉን አገር ወዳድ የሽግግር ሂደት ለማምከን የሚደረገውን ጥረት ሁሉ ውጤት አለባ ማድረግ ያስፈልጋል ። ግዴታ ነው ። አፋቸውን አውጥተው ወያኔን ሳይሆን አሜሪካ ይደግፈናል ማለት የጀመሩትንም ስምሪት ነቅቶ መከታተል ጊዜ ነው ።

ይህን ካልን ዘንዳ እስቲ የሚከተሉትንም በግንዛቤ እናስገባቸው፤

- ወያኔ ሕጻናትን ለባዕዳን በመሸጥ ብዙ ሚሊዮን ዶላር እያስገባ ነው ተባለ ፤
- ድርቁና ረሃቡ እየተስፋፋ እንጂ ይመጣል የተባለው እርዳታ እየመጣ አለመሆኑን ከአፋሮች አካባቢ ከቀንድ ከብት በብዛት መሞትና ህጻናትም መጠቃት ተያይዞ የቀረበው መረጃ ግልጽ አድርጓል ።ወያኔ አሁንም ለረሀብተኛው እርዳታ አያለ ወደ ኪሱና ካዝናው እየከተተ ነውም ተብሏል ።
- ኖርዌይ ከወያኔ ተስማምታ ወደ 800 ስደተኞችን እመልሳለሁ ያለችውን በመቃወም ኢሕአፓ ለጠቅላይ ሚኒስቴሩ የተቃውሞ ደብዳቤ ጻፈ ።
- በጅቡቲ በተቃዋሚዎች ላይ በተለይ በታጁራና አሳል ሀይቅ አካባቢ አፈናው ተጠናክሯል ሲባል ወያኔ ደግሞ ተቃዋሚውን ፍሩድ ድርጅት በ ሻዕቢያ የሚደገፍ ሲል ከሷል ። ፍሩድ በበኩሉ የወያኒን ክስ ውሸት ብሎታል ።

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

## ምን ይሰማ……አገር?



**“ ድሬዳዋ ከተማ አሳ ዘነበ፤”**
*(በ፳፻፲፰ ጃንዋሪ መጨረሻዉ ላይ የተለያዩ ድረ ገጾች ያስነበቡት ዜና፤)*

- **ድርቅና ረሃብ መድረሻ አጡ በሉና !! ….ግን ይኼኛዉ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ተዓምር በአለፉት ዓመታት በተከታታይ ከታየዉ የ፲፩ በመቶ ( 11%) ዕድገት ዉጪ የተገኘ መሆኑን ዓለም ያዉቀዋል ?! …. ሔሎ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን!!**

//

**“ ዲሞክራሲ ለአፍሪካ ቅንጦት ነዉ ።”**
*(ኃይሌ ገ/ ሥላሴ ለቢቢሲ ከሰጠዉ ቃለመጠይቅ የተቀነጨበ የአፍ ወለምታ።)*

- **ሆዱን የወደደ ማዕረጉን የጠላ ነዉ፤” ይባላል ። ከሕዝብ ከበሬታ ወርቅ ያበለጠም ያዉ ነዉ ። ግን ግን ኃይሌ….የወርቅ ማዕድኑ ትግራይ ዉስጥ ነዉ እንዴ የሚገኘዉ?**

//

**“ የአባይ ፀሐዬ የለሁበትም የት ያደርስ ይሆን ?!”**
*(የቀድሞዉ የፓርላማ አባ፤ል ግርማ ሰይፉ በተለያዩ ድረ ገጾች ያስነበቡት መጣጥፍ ርዕስ።)*

- **ሲሆን ሲሆን ከርቸሌ ፤ ሳይሆን ሳይሆን ዚምባብዌ እንበልዎት?!**

//

**“ የወያኔ ጸባይ እኛን መተንበይ የማንችል መሪዎች አድርጎ ነው ያስቀመጠን ።”**
(የመድረኩ ቁንጮ በየነ ጴጥሮስ ( ዶ/ር ) የሰጡት ቃለ መጠይቅ ጨመቅ ፤ ሪፖርተር ጋዜጣ በጃንዋሪ ፴ ዕትሙ እንዳስነበበዉ።)

- **ራስን መገምገም ይሏል ይህ ነዉ - ከድፍን ሀያ አራት ዓመታት በኋላ ! ----ደግነቱ ዛሬም ራስዎን መሪ ( ፕሬዚዳንት ) ብለዉ መጥራትዎ ይገርመናል።**

//

**“ እኔ ባለሁበት 99% ሙስሊም ነዉ ። ስለዚህ ማንም ሰዉ ደፍሮ ቀና አይልም፤ በሜንጫ አንገቱን ነዉ የምንለዉ ።”**
(“ጃዋር መሀመድ የተናገረዉን በመጥቀስ በፌስ ቡክ ከተሰራጨ ጽሁፍ የተወሰደ። )


- **የአባዱላ የካድሬዎች መረብ እስከ ሰሜን አሜሪካ መዘርጋቱን ከተረዳን ቆየን ። …አንገት መቀንጠስ ካማረህ እዚህ ምን ታደርጋለህ ? የወያኔን ቱልቱላ በሩቅ ከምትነፋ፤ የጃራ አባገዳ ሐዋርያነትህን ለማረጋገጥ አዋሽን መሻገሩ አይቀልልም ?**

ከገጽ 1 የዞረ

- ዓለም አቀፍ የፋይናንስ መረጃ (ግሎባል ፋይንሺያል ኢንተሊጀንስ) የተባለው ተቋም እንዳጋለጠው ከሆነ በየዓመቱ ከኢትዮጵያ ሁለት ቢሊዮን ዶላር በህገወጥ መንገድ የሚወጣ መሆኑን አጋልጦ ከአውሮጳውያን አቆጣጠር ከ 2004 ዓ.ም. እስከ 2013 ዓ.ም. ድረስ ኢትዮጵያ 26 ቢሊዮን ዶላር መዘረፏን አጋልጧል። የወያኔ ባለስልጣኖች ይህን ያህለ ገንዘብ አልወጣም እያሉ ሰበብ ሲደረድሩ የቆዩ ሲሆን መለስና ቤተሰቡ ከ 2 ቢሊዮንን ዶላር በላይ መዝረፋቸውን በባሃማስ፤በስዊስ፤በሳውዲ፤በማሌዚያ ወዘተ.. ባንኮች ማስቀመጣቸው የሚታወቅ ነው ተብሏል ። በከፍተኛ ደረጃ ያለ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ከዚሁ ጋር ተያይዞም የመጣ መሆኑ ተጠቅሷል ። የህገ ወጥ ገበያ መድራትን በማንሳት ወያኔ ሰበብ ቢፈልግም በብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ ደብዛው የጠፋበት ምክንያት የወያኔ መሪዎችና ባለስልጣኖች ገንዘቡን ወደ ውጭ ስላሸሹት ነው በማለት ምክንያት የሚሰጡ በርካታ ናቸው ።

- ወያኔ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የሃይማኖት ተቋማትን በአጠቃላይ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን እና የእስልምና እምነትን በተለይ በቁጥጥሩ ስር አድርጓቸዋል፡፡ በኃላፊነት የሚሾሙ የወያኔ አባል መሆናቸው የግድ ከሆነ አመታት ተቆጥረዋል፡፡ ለእምነት ተቋሞቻቸው ከምእመናንና ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የሚገባው ገንዘብ እንዳለ ይዘረፋል፡፡ ይህ የሚዘረፈው ገንዘብ እስከ ከፍተኛዎቹ የወያኔ መኳንንቶች ድረስ ይጓዛል፡፡ በየሃይማኖት ተቋማቱ በኃላፊነት የሚቀመጡ ሁሉ የወያኔ ካድሬዎች ስለሆኑ ዋናው ተግባራቸው የወያኔን የዘር ፖለቲካ ከሀይማኖት አስተምህሮት ጋር በማስተሳሰር መስበክና በዘር፣ በጎጥ፣ በዘምድና እና በገንዘብ ሰዎችን መቅጠር ሲሆን የየሀይማኖቱን ገንዘብ መዝረፍ እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡ ሌብነታቸውን ለመሸፈን እንደ ፖለቲካ ካድሬ ይደነፋሉ፡፡ ከሁለት በላይ ቤትና መኪና የሌለው የሃይማኖት አስተዳዳሪ እንደማይገኝ የሚያስረዱ ብዙዎች ናቸው፡፡ አልፎ አልፎ በአንዳዶቹ ላይ ርምጃ ሲወሰድ የሽፍትነት አጸፋ እርምጃ ይወስዳሉ፡፡ ባለፈው ታህሳስ 26 ቀን 2008 ዓ.ም. አንድ በሌብነቱ ከነበረበት ኃላፊነት ዝቅ የተደረገ የደብረ ብርሀን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀገረ ስብከት አስተዳደር ክፍል ኃላፊ ከደረጃው ዝቅ እንዲል በመደረጉ በሊቀ ጳጳሱ መኖሪያ ቤት አጠገብ ቦምብ እንደወረወረ የሚታወቅ ነው፡፡ ቦምቡ እቢሮው ውሲጥ የነበሩ ሰነዶችን ለማቃጠልና ውሳኔውን የሰጡት ጳጳስ ላይም እንደተቃጣ የአካባቢው ካህናትና ምእመናን ያስረዳሉ፡፡ እንዲህ ያለ የወሮ በላ ተግባር እየተስፋፋ እንደሚሄድ ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ ወገኖች ስጋታቸውን ይገልጻሉ፡፡

Rose Unisex Hair Salon (Tsegereda)
6222 Georgia Ave. NW Washington, DC. 20011



የሴቶችንና የወንዶችን፣ የልጆችንና የአዋቂዎችን ፀጉር እናስተካክላለን። ለቀለም ፣ለሹርባ፣ ለፀጉር ስፌትና ለፐርም ሰራ ባለሙያ ከፈለጉ Rose Unisex Hair Salon (Tsegereda)

- ህዝብን አሸብሮ መግዛት በሚለው ፈሊጡ አሸባሪው ወያኔ በአርሲ ሻላ፣ ሲራሮ፣ ሻሸመኔና ዞዋይ እና በሐረርጌ ግራዋ የሕዝብን ደም አፈሰሰ፡፡ በሁሉም አካባቢዎች ሕዝቡን ለአመጽ ያነሳሱት ምክንያቶች በጥቅሉ ወያኔ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን ግፍ በመቃወም እንደሆነ ከአካባቢዎቹ ከሚወጡ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ በአርሲ በአንድ የሠርገኛ አጃቢ መኪና በወያኔ የተከለከለ የኦሮምኛ ዘፈን በማዘፈኑ የፌደራል ፖሊስ ዩኒፎርምን የለበሱ የአጋዚ ጦር አባላት ሙሽሮቹ ላይ ተኩስ በመክፈታቸው የተነሳው ግጭት ይህ ዘገባ እስከ ተጠናከረበት ጊዜ ወደ ሃያ የሚጠጉ የጋአጋዚ ጦር አባላት በቁጣ በተነሳው ሕዝብ መገደላቸው ታውቋል፡፡ የወያኔው አጋዚ ጦርም ያገኘውን ሰው ሁሉ በማሰር የተወሰኑትን በመቀጣጫ ስም የረሸነና በጅምላ መቃብር የቀበራቸው መሆኑ ከአካባቢው ኗሪዎች እየተነገረ ነው፡፡ ሐሙስ የካቲት 9 ቀን አመሻሽ ላይ በዞዋይ በተቀሰቀሰ አመጽ ወደ አምስት የሚጠጉ መኪናዎች እንደተቃጠሉና ቦምብም እንደተወረወረ ከታመኑ ምንጮች የተገኘው ዜና ያስረዳል፡፡ በግራዋና አካባቢዋም ሕዝቡ መብቱን ለማስከበር በወያኔ ላይ እያደረገ ባለው አመጽ በርካታ ንጹሀን ዜጎች እንደተገደሉና እንደታሰሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዐርብ ሕዝባዊው አመጽ በአምቦና በጉደር በከፍተኛ ሁኔታ መካሄዱን ከአከባቢው ኗሪዎች ተረድተናል፡፡ በሁሉም ሕዝባዊ አመጽ በተቀጣጠለባቸው አካባዎች ሕዝቡ በወያኔ ካድሬዎች መኖሪያ ቤቶች ላይና በመንግስት መሥሪያ ቤቶች ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡ በሻሸመኔ ወያኔ የተቀሰቀሰውን ድርጊት በሙስሊሞች ላይ አላኮ ሙስሊሞችን ነጥሎ ለማጥቃት ያደረገውን ሙከራ ሕዝቡ አከሽፎታል፡፡ ሞስሊሞችና ክርስቲያኖች በአንድነት በወያኔ ላይ በማመጻቸው የአካባቢው የወያኔ ካድሬዎችና ደህንነቶች እንደተደናገጡ ከአካባው ምንጮቻችን ተረድተናል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አሜሪካ፣ እንግሊዝና ኖርዌ ዜጎቻቸው እንቅስቃሴዎቻቸውን በጥንቃቄ እንዲያደርጉ መግለጫ ማውጣታቸው ታውቋል፡፡

- ሰላሳ ዓመት ዩጋንዳን ሲገዛ የባጀው ዮዌሪ ካጉታ ሙሴቬኒ ህግ በማይፈቅደው መሰረት ለ 5ኛ ጊዜ ለምርጫ ቀርቢያለሁ በሚል ያው በተጭበረበር ሁኔታም አሸናፊ ሆኛለሁ ብሎ ተሰይሟል ። ተወዳዳሪዎቹንም አስሯል። ነጻ ምርጫ ቢካሄድ ሙሴቬኑ የማያሸንፍ መሆኑን ብዙዎች ቢያምኑም ይህ በአሜሪካና እንግሊዝ የሚደገፍ መሪ አምባገነናዊ አገዛዙን ሊቀጥል ተዘጋጅቷል ። የዩጋንዳን መከላከያ ጦር የሚቆጣጠረው ወንድሙ ጄኔራል ሳሌም ሳሌህ ሲሆን ልዩውን ጦር ደግሞ ሀላፊ ሆኖ የተሰየመው የራሱ ልጅ ነው ። የምርጫ ቦርዱም ነጻ ሳይሆን ለሙሴቬኒ ታዛዥ ነው ሲባል አገዛዙ በሙስና መበከሉን ደግሞ ዓለም አቀፍ ሀይሎች የዘገቡት ነው ። ጄኔራል ሳሌም ሳሌህ ከካሳ ከበደ ጋር ሆኖ ከእስራኤል የጦር መሳሪያ መግዛት በሚል ብዙ ሚሊዮን ዶላር ለግሉ መውሰዱን ውስጠ አዋቂዎች ቀድም ሲል ማጋለጣቸውም ይታወሳል ። ሙሴቬኒ እያጭበረበረ በስልጣን መቀጠሉ ዩጋንዳን ወደ እርስ በርስ ብጥብጥ ያመራታል ሲሉ ታዛቢዎች ጠቁመዋል።

- የወያኔ አገዛዝ ፕራቬታይዜሽን በሚል ፖሊሲ የመንግስት ሀብት የነበሩትን ተቋሞች ለግል ሀብታሞች የሸጠ ቢሆንም እስካሁን ድረስ በርከት ያለ የሽያጭ ገንዘብ ያላሰባሰበ መሆኑ ታወቀ። ለዚህ ጉዳይ ወያኔ ያቋቋመው ተቋም 34 የሚሆኑ የንግድና የማምረቻ ተቋሞችን በ2.15 ቢሊዮን ብር የሸጠ ሲሆን እስካሁን ያስገባው 8.6 ሚሊዮን ብር ብቻ ነው። የአልአሙዲው ንብረት የሆነው ሜድሮክ ኩባንያ 1.5 ቢሊዮን ብር ያልከፈለው እዳ ያለበት ሲሆን ይኸው ካጠቃላዩ ውስጥ ስድሳ ከመቶ የሚሆነው መሆኑም ተዘግቧል። የመንግስትን ንብረት ለግል ባለሃብቶች መሸጥ በሚል ሽፋን የወያኔ ባለስልጣኖች በርካታ የሕዝብ ሀብት የዘረፉ መሆናቸው የአደባባይ ሚስጥር ነው የሚሉ በርካታ ናችው።

- የመተማ ዮሀንስ ሕዝብ በተደጋጋሚ አቤት ቢልም እስከ አሁን ምንም ዓይነት የስልክ አገልግሎት እንደማይገኝ የታወቀ ነው፡፡ በዚህ ከተማ ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ ወደ ሰማንያ ሺ እንደሚጠጋ ይገመታል፡፡ ከመተማ ዮሀንስ ወደ መሀል አገር የሚደረግ የስልክ ግንኙነት በቀጥታ በኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን በኩል ስላልተቻለ በሱዳን በኩል መሆኑ የግድ ሆኗል፡፡ በዚህ ሳቢያ ሕዝቡ የሱዳንን የስልክ አገልግሎት እንዲጠቀም በመደረጉ ለከፍተኛ ወጪ መዳረጉን የከተማዋ ኗሪዎች በምሬት እየገለጹ ነው፡፡ ብዙዎች እንደሚሉት ይህ ወያኔ በህዝብ ስቃይ ሱዳንን ለመጥቀም ያደረገው ደባ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በርካታ የፖለቲካ ተንታኞች አገርን ቆርሶ ለጊዚያዊ የፖለቲካ ጥቅም የሸጠ ጠባብ ቡድን የመተማን ሕዝብ በባእዳን ማስበዝበዙ ቢያበሳጭም ባህርዩ መሆኑ ሊሳት አይገባውም ይላሉ፡፡

ከኢሕአፓ ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም የቻላል

| | |
|---|---|
| ስልክ፡ | (202) 291-4217 |
| ኢሜል፡ | espic@aol.com |
| ፖስታ፡ | EPRP<br>P.O. Box 73337<br>Washington, DC. 20056 |
| ድረ ገጽ፡ | eprp.com |

ፍኖተ ዴሞክራሲን ለማዳመጥ Finote.org

ከኢሕአፓ ወክንድ (EPRPYL) ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም የቻላል

| | |
|---|---|
| ስልክ፡ | (202) 291-5832 |
| ኢሜል፡ | eprpylnew@gmail.com |
| ፖስታ፡ | EPRPYL<br>5309 Georgia ave.<br>Washington, DC. 20011 |
| ድረ ገጽ፡ | eprpyl.com |

# ትናንትና

**ካለፈዉ የቀተለ**

## በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤
## የጓድ ቆንጂት ተክሉ ክራሞት

## 4

የህቡዕ ትግል ብርታቱና ጥንካሬዉ ያለዉ ብቻ በህይወት የሚቀጥልበት ዓለም ነዉ ። አንድ ሰዉ በህቡዕ ዓለም ውስጥ የሚኖረዉ ዕድሜ ርዝማኔ በግሉ ባለዉ ቅልጥፍና ፤ብቁነት ፤ወኔና ራሱን በየጊዜዉ ከሚፈራረቁት ሁኔታዎች ጋር ለማለማመድ ባለዉ ችሎታ ልክ ይወሰናል ። ጥሩ ተመልካች መሆን የሚገባዉን ያህል መልካም ተማሪም መሆን ይኖርበታል። ከግል ህይወት ቀጥተኛ ተሞክሮም ሆነ ከሌሎች ስኬትና ድክመት የሚቀሰም ትምህርት እጅጉን ጠቃሚ ነዉ ።

በዚህ ረገድ ፤ በአንድ ወቅት አብራኝ ትሠራ ከነበረች አንዷት ወጣት ሴት የቀሰምኩት ትምህርት ይታወሰኛል። ወጣቷ በሙሉ ጊዜ ሙያዋ በህቡዕ የምትታገል አብዮታዊ ብትሆንም መታወቂያ የወጣለትና በሌሎችም አስፈላጊ ሰነዶች የተደገፈ ሕጋዊ ኑሮ በመኖር ላይ ነበረች ። በዘመኑ አለባበስ አምራና ተሽቀርቅራ ዕለታዊ ሥራዋን ታካሄዳለች። ይሁንና ድብቁ ማንነቷ ተነቅቶበት ኖሮ ፤ እርሷ ሳታዉቀዉ የደርግ ፖሊሶች በስዉር ይከታተሏት ጀመር ። በራሷ ከሚገባዉ በላይ በመተማመኗና ቄንጠኛዉ አለባበሷና ሁለነገሯ የሌሎችን ትኩረት እንደማይስብባት በርግጠኛነት በማመኗ የተነሳ ያለአንዳች ልዩ ጥንቃቄ በተለመደዉ ሥራዋ ገፋችበት። ተለምዶዋን አልቀየረችም ፤ የአሠራር ዘይቤዋንም አላፈራረቀችም። የደርግ ፖሊሶች ረዘም ላለ ጊዜ ሳያስነቁ ተከታተሏት ። የምትገናኛቸዉን ሰዎች አንድ በአንድ ፎቶ አነሱ ፤ የቤቷንና አዘዉትራ የምትጠቀምባቸዉን የህዝብ ስልኮች ጠለፉ ፤ ከሌሎች ጋር በቀጠሮ የምትገናኝበትንና ለስብሰባ የምትጠቀምባቸዉን ሥፍራዎች ለይተዉ አወቁ ፤ …ወዘተ። ሁኔታዋ ሁሉ ከብረት ፍርግርግ በተሠራ ትልቅ ጎጆ ዉስጥ እየኖረች በምናቧ ግን ራሷን ነጻ አድርጋ ከምትስል ወፍ ጋር የሚመሳሰል ነበር ። በደርግ የስለላ መዋቅር ዉስጥ የተተከለዉ አንድ ወገን ስለሁኔታዉ በጊዜ ሊያስታዉቅ በመቻሉ ድርጅታችንን ከትልቅ መዓት ሰዉሮታል ። በዚያ ፖሊሳዊ ክትትል የተደረሰባቸዉ ጓዶች በጊዜ ወደ ሌላ ሥፍራ ከመዘዋወራቸዉም በላይ ለአደጋ የተጋለጡ ድርጅታዊ ህዋሳት እንዲበተኑ ተደርጓል ። ወጣቷ ሴትና ከርሷ ጋር ይገናኝ የነበረ አንድ ሌላ ሰዉ ብቻ (እነርሱንም ቢሆን በጊዜ ልንገናኛቸዉና ስለሁኔታዉ ልናሳዉቃቸዉ ባለመቻላችን የተነሳ፤) ነበሩ ከደርጉ ደህንነት እጅ የወደቁት ።

ከተሞክሮዉ በቀሰምኩት ትምህርት መሠረት፤ በህቡዕ ለሚንቀሳቀስ ማንኛዉም ሰዉ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች አንዱ ንቁ አስተዋይ ( ተመልካች ) ሆኖ መገኘት ነዉ ። ተራ የሆነ አሠራርንና በገዛ ራስ ድምዳሜ የመርካት አባዜን ማስወገድም ጠቃሚዉ ነዉ ። ከአካባቢ ጋር ራስን አመሳስሎ የመዋሀድ ፤ የሌሎችን አትኩሮት ያለመሳብና የሚያንዣብብን አደጋ ከሩቁ የማሽተት ክሂሎት ሊኖረዉም ይገባል ። በህይወት ዉስጥ፤ ይበልጡን ደግሞ በትግል ላይ አዘዉትሮ እንደሚታየዉ የገዛ ራስ ጥንካሬ እጅጉን ጠቃሚ መሆኑ ባያጠያይቅም ብቻዉን ለስኬት አያበቃም ።የጠላት ድክመትም የገዛ ራሱን ሚና ይጫወታል። ማንኛዉም ጨቋኝ አገዛዝ ደግሞ ተቃዋሚ ታጋዮች ስኬት አስተዋጽዖ ሊያበረክቱ የሚችሉ አያሌ ደካማ ጎኖችና ስህተቶች አሉት ። በአገዛዙ የደኅንነት ተቋም ዉስጥ ከሚገኙት ሠራተኞች መሀከል አብዛኛዎቹ ለአገዛዙ በታማኝነት የማያገለግሉ የመሆናቸዉ ዕዉነታ ለእኛ አመቺ ነበር ። በደኅንነቱ መዋቅር ዉስጥ የተሠማሩትን የደርግ የመረጃ ሠራተኞች ለመመልመል ከመቻላችንም በላይ ከከፍተኛዎቹ የሥልጣን ዕርከኖች ላይ ሳይቀር ስዉር ሰርጎገቦችን ለመትከል በቅተናል።

ይህን መሰሉ ሁኔታ ፤ ያን ያህል ወሳኝነት ባይኖረዉም እንኳ ፤ እንቅስቃሴዎቻችንን በማቀለጣጠፍ ረገድ የበኩሉን ድርሻ ተጫዉቷል ።የደርጉ አገዛዝ እጅግ ዐረመኔያዊ ወደሆነዉ ግብሩ (ብዙኀኑን የኅብረተሰብ ክፍሎች -ማለትም፤ ተማሪዎችን፤ የቢሮና የፋብሪካ ሠራተኞችን ፤ የመንግሥት ሠራተኞችን ፤ ወዘተ….) በጅምላ እያፈሰ ለወራት እስራት ማጋዝ ወደጀመረበት ዘመቻ ከመሸጋገሩ አስቀድሞ በገዛ አባላቱ ላይ የማስወገድና የኃይል ርምጃዎችን መዉሰድ ግድ ብሎት ነበር። እነዚህን መሰሎቹ የአገዛዙ አካላት ላሳዩት ዳተኛነት መንስዔዉ በግልጽ ከሚታወቀዉና ከነበረን ሕዝባዊ ድጋፍ ሌላ ስለወታደራዊ ጥንካሬያችን የነበራቸዉን እጅጉን የተጋነነ ግምት የተመረኮዘ ፍርሃትን ያዳበለ ነበርና ድርጅታዊ እንቅስቃሴዎቻችንን እንዳሻን ለማካሄድ ተገን ሆኖናል ።

ትዝ ይለኛል ፤ አንድ ጊዜ በትጥቅ የታገዘ ቅስቀሳ በሚያደርጉ ቡድኖች አማካይነት አደባባዮች ላይ የሚሰቀሉ የድርጅታችንን ስምና ዓርማ የያዙ ሰንደቆችን የማዘጋጀቱ ኃላፊነት እኔ ለምገኝበት ህዋስ ተሰጠ። በወቅቱ ቀይና ቢጫ ቀለም ያላቸዉን የጣቃ ጨርቆች ፤ ወረቀቶችን ወይም ቀለሞችን የሚገዛ ማናቸዉም ሰዉ ከተጠርጣሪነት አይድንም ነበርና ተፈላጊዎቹን ቁሳቁሶች ለማግኘት ፈጠራ የታከለባቸዉን ዘዴዎች መጠቀም ነበረብን ። ወርድና ቁመቱ ሁለት ሜትር በሦስት ሜትር የሆነዉን ከናይለን ጨርቅ የተዘጋጀ ዓርማ ሰፍቶ ለማጠናቀቅ ሦስት ምሽቶች ወሰደብን ። ከናይሎኑ ዓርማ የማንጠልጠያ ገመዶች ላይ ክብደት ሰጪ ቁስ የታከለበትን የሥራችንን ዉጤት በትጥቅ ታግዞ ቅስቀሳ ለሚያደርገዉ ቡድን ለማስረከብ እኔ ተመደብኩ ። ከቡድኑ ጋር የግንኙነት ቀጠሮና ሥፍራ ካዘጋጀሁ በኋላ ዓርማዉን በዘንቢል ከትቼ በመያዝ ከቡድኑ ጋር ለመገናኘት አመራሁ።

የተሰጠኝ ኀላፊነት ቀላል የሚመስለዉን ያህል የቀለለ አልነበረም። በእነዚያ ጊዜያት የከተማይቱ ጎዳናዎች ሁሉ በደኅንነት ሠራተኞችና ፖሊሶች ቅኝት ሥር የነበሩበት ፤ ሁኔታዉም ዉጥረት የነገሠበትና አደገኛ ነበር። ፓርቲያችን የታወጀበት የሁለተኛ ዓመት በዓል በመቃረቡ የተነሳ ጥቃቅኗን ዕለታዊ እንቅስቃሴ ሁሉ በተጠንቀቅ ሆነዉ መከታተል ነበረባቸዉ ። ነሀሴ ፳፭ ቀን ( አገስት 31 ወይም ሴፕቴምበር አንድ) ዓርማዎቻችንንና ፖስተሮችን በመላዉ አዲስ አበባ እንደምናሰራጭ አዉቀዉ እየተጠባበቁን ነበር። በበኩላችን እነርሱ ባልጠበቁት መንገድ በተመረጡ ሥፍራዎች የተወሰኑና በተቻለዉ መንገድ የሕዝብን አትኩሮት በሚማርክ አቀራረብ "አጀብ ጉድ" ልናሰኛቸዉ ወስነን ነበር የተነሳነዉ ። በዚህ መሀከል ፤ እንድገናኘዉ ተልዕኮ ተሰጥቶኝ የተሰማራሁበት የታጥቆ ቀስቃሽ ቡድን በሌላኛዉ የከተማ ክፍል ከሚገኝ አንድ የቤንዚን ማደያ ፤ ንብረትነቱ የመንግሥት የሆነ አንድ አነስተኛ የሕዝብ መጓጓዣ መኪና ( ቫን ) ከነነጂዉ ከጠለፈ በኋላ ነጂዉን ወደ አንድ ቡና ቤት ወስዶ አግቶት ኖሯል ።በእኔ በኩል ፤በቀጠሮዬ ሰዓት ዘንቢሌን ይዤ ወደ አንድ አነስተኛ ሱቅ ( ኪዎስክ) ካመራሁ በኋላ የግንኙነታችንን ማመስጠሪያ (ኮድ ) በእጁ ከያዘ አንድ ሰዉ አጠገብ አስቀመጥኩት ። ሰዉየዉም ወዲያዉኑ ዘንቢሉን ከተቀመጠበት አንስቶ ዘወር አለ።

ለቅኝት አመቺ ከሆነ ሥፍራ ሆኜ ዙሪያ ገባዉን እመለከት ጀመር ። ያደረግነዉን አንድም ሰዉ የተመለከተ አይመስልም ።እናም ቀጥሎ የሚከናወነዉን ድርጊት እጠባበቅ ጀመር። ከቀትር በኋላ ልክ ስምንት ሰዓት ተኩል ሲሆን ፤ ከአፍ እስከገደፋቸዉ ተሳፋሪዎችን ያጨቁ አቶቡሶችና መኪኖች በባለአራት መሙ የቸርችል ጎዳና በሚተምሙበትና አካባቢዉ በሚጨናነቅበት ጊዜ ታጥቆ ቀስቃሹ ቡድናችን የተሰጠዉን ተልዕኮ ጀመረ ። ለተልዕኮዉ መከናወኛ የተመረጠዉ ቦታ በከተማዉ ዉስጥ እጅግ ታዋቂ ከሆኑት ሥፍራዎች አንዱ የሆነዉ የቴዎድሮስ አደባባይ ሲሆን ኩታ ገጠም በሆኑ ሁለት ከፍተኛዎች ዉስጥ የሚገኙ አራት ቀበሌዎች ( ማለትም ከከፍተኛ ፪ -ቀበሌ ፲፰ እና ቀበሌ ፲፯ ፤ ከከፍተኛ ፫ ደግሞ -ቀበሌ ፲፬ እና ቀበሌ ፴፫ ) ይዋሰኑታል ። ለተልዕኮዉ ክንዉን ተስማሚ በሆነ ቅጽበት ፤ ቀዩ የትራፊክ መብራት በርቶ የጎዳናዉን የመኪኖች ፍሰት ሲያስቆም ቀደም ብሎ የተጠለፈዉና ቡድኑ የሚገለገልበት መኪና (ቫን) ከመቅጽበት ፊቱን በማዞር የአደባባዮን ገሚስ መንገድ በአግድመት ዘግቶ ቆመ ።

ወድያዉኑም ፤ የፊት ጭምብል ያጠለቁት የታጥቆ ቅስቀሳዉ ቡድን አባላት ከመኪናዉ ዘለዉ በመዉረድ ቦታ ቦታቸዉን ከያዙ በኋላ የአደባባዩን ትራፊክ ሙሉ በሙሉ ዘጉት ። ለቡድኑ ደኅንነት ሽፋንየሚሰጡ አሀዶችም ሥፍራቸዉን ይዘዉ ዝግጁ ሆነዉ መጠባበቅ ጀምረዋል። እዉነቱን ለመናገር እጅግ ድፍረት የተመላዉ ድርጊት ነበር ። ካለሁበት ሆኜ በጓዶቻችን የተከፈተዉ የቴፕ ማጫወቻ የሚያስደምጠዉ "የትግሉ ነዉ ህይወቴ"´መዝሙር ጣዕመ ዜማ ይሰማኛል። ሁለት የቡድኑ አባላት የድርጅታችንን ዓርማ በማዉጣት አገዛዙ በየዓመቱ ሥልጣን ላይ የተቆናጠጠበትን ዕለት ለማሸብረቅ ከሚጠቀምበት ቅስት ላይ ሰቀሉት ።በጣም የሚመች ሁኔታ ነበር ። ዓርማዉን ቅስቱ ላይ ለመስቀልና ለመወጠር ከተገለገሉባቸዉ የናይሎን ገመዶች ጫፎች ላይ በተንጠለጠሉት ክብደት መስጫ ቋጠሮዎች ላይ ዓርማዉን መንካት የከፋ መዘዝ እንደሚያስከትል የሚያስገነዝቡ ማስጠንቀቂያ ምልክቶች ተደርገዉባቸዋል ።

በጥቅሉ ሲታይ፤ በትዕግርምት የተዋጡ በመቶዎች ለሚቆጠሩ እግረኞች፤ ለግል መኪኖችና የአቶቡስ ተሳፋሪዎች ግልጽ ዕይታ የበቃ በሚያስገርም ፍጥነትና ቅልጥፍና የተፈጸመ ክንዋኔ ነበር ።ለእኔ ግን፤ ተልዕኮዉ የተጠናቀቀባቸዉ እነዚያ ጥቂት ደቂቃዎች የሰዓታት ያህል ረዝመዉ ነዉ የተሰሙኝ ። በአካባቢዉ በርካታ የቀበሌ ዘበኞች ነበሩ ። ከነዚሁ ዉስጥ አብዛኛዎቹ የኛዉ ደጋፊዎች በመሆናቸዉና የተቀሩትም በተልዕኮአችን ድንገተኛነትና ቅልጥፍና ደንዝዘዉ ርምጃ ሳይወስዱብን ቀርተዋል ።ኋላ ላይ እንደሰማነዉ፤ የአካባቢዉ የቀበሌ ጥበቃዎች ድርጊቱ የተፈጸመበት የቴዎድሮስ አደባባይ ከክልላቸዉ ዉጪ መሆኑን በማመካኘት የገዛ ራሳቸዉን በሀላፊነት ከመጠየቅ ተከላክለዋል ። ያም ሆነ ይህ ፤ ዓርማችን ተሰቅሎ ከተዉለበለበ ከሀያ (፳) ደቂቃዎች በኋላ ጥቂት "ቆራጥ" የከፍተኛዎቹ የጥበቃ አባላትተሰባስበዉ ዕይታውን የማይሹትን ዓርማ ለማዉረድ ከበባ ማድረጋቸዉ አልቀረም ። ይሁን እንጂ ፤ ዓርማዉን መንካቱ መዘዝ የሚያስከትል መሆኑን የሚያመላክተዉን ማስጠንቀቂያ በማየታቸዉ ከርምጃቸዉ ተገቱ። ተጣድፈዉ በተሰባሰቡበት ፍጥነት ልክ ፤ የፈንጂ አምካኝ ቡድን ወደ ሥፍራዉ እንዲላክ በስልክ ለመጠየቅ ወስነዉ ሲያፈገፍጉ መመልከት በራሱ ሣቅ ያጭር ነበር ። የሃሰትም ቢሆን ፤ የቦምቡ ማስፈራሪያ የታቀደለትን ጥቅም አስገኝቶ የድርጅታችን የኢሕአፓ ዓርማ በአየር ላይ የሚዉለበለብበትን ተጨማሪ ጊዜ ሊያስገኝ በቅቷል ።

የህቡዕ ሕይወቴ ይህን በመሳሰሉና በመቶዎች በሚቆጠሩ ተግባራትና ተሞክሮዎች የተመላ ነዉ ።ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት፤ ፋሺስታዊዉን አገዛዝ የእግር እሳት ሆነዉ የሚያቃጥሉ በርካታ ሺህ እኔን መሰል ታጋዮች አሉ። ከተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ፤ በተለይም ከጎስቋሎቹ ጋር በጥብቅ ተሳስረናል ። በነርሱ ታቅፈናልም ። ይህ መቼም የኢሕአፓ ጠላቶች እንኳ ሊክዱት ያልቻሉት ሀቅ ነበር። ድርጅታችን ኢሕአፓ በአብዛኛዉ ሕዝብ ዘንድ ይፈቀርና ድጋፋቸዉንም ያገኝ ነበር። ሕዝቡ በበርካታ መንገዶች ተገን ሆኖ ይንከባከበንና ያበረታታን የነበረ ሲሆን ከትግሉ ጋር ተደባልቋል ። እነዚሁ ወገኖቻችን ፤ ዞሮ ዞሮ የገዛ ራሳቸዉ ጉዳይ ለሆነዉ ታላቅ ዓላማ በትግል ለምንከፍለዉ መሥዋዕትም ከፍተኛ ግምት ነበራቸዉ ።

ይህን መሰሉ ፤ በሕዝቡና በድርጅቱ መሀከል የነበረዉ ተምሳሌያዊ ተዛምዶ ነበር አገዛዙን ከሁሉም በላይ ያሳስብ የነበረዉ ። እየተስፋፋ የሄደዉና ወገን ሳይለይ ይካሄድ የነበረዉ መንግሥታዊ ግድያና ሁለ-ገብ የኃይል እመቃ ሁሉ ዞሮ ዞሮ ዓላማዉ ይህንኑ ሕዝባዊ ተዛምዶ የመስበር ሲሆን የ"ቀይ ሽብር" ዘመቻና ከዚያ በፊትም ሆነ በኋላ የተወሰዱት የጭፍጨፋ ርምጃዎች በሙሉ ለዚሁ ግብ የታቀዱ ናቸዉ።

እዚህ ላይ ፤ወደ ዋናዉ የትረካዬ አቅጣጫ በመመለስ የፋሺስታዊዉ አገዛዝ የጅምላ ዕመቃ ዘመቻ እንደምን እንደተካሄደ የዓይን እማኝነቴን ዘገባ ለማቅረብ እሞክራለሁ ።

**ይቀጥላል……..**

## ዓለምና ዘመን ፊታቸውን ያዞሩባት ሀገር !

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
ጥር 9 ቀን 2008 ዓ.ም. የተላለፈ ሐተታ

በዘረኝነት ላይ የተመሰረተ አምባገነን አገዛዝ በኢትዮጵያ ከተንሰራፋ ፤ይኸው ሠላሣ ዓመታት እያስቆጠረ ነው። በዘመን ስሌት ሲቆጠር ቀላል ጊዜ አይደለም ። የአንድ መሥዋዕታዊ ትውልድ ዘመን አሳልፎ ሌላ ትውልድ እየተካ ይገኛል ። ይህ ዘመን ፤ በሀገራችን ታሪክ ዜና መዋዕል፤ የመከራ፤ የውርደት፤ የሀፍረት፤ የጥፋት፤ የጥቃት፤ ሀገር የመቆራረስና ሕዝብ የመከፋፈል ሀቅን መዝግቧል ። በዚህ ዕኩይ ዘመን፤ የሀገሪቱ ዳር-ድንበር ተደፍሯል ። ሀገራዊ ወሰኗ የት ላይ እንደሚቆም እንኳን ገና አልታወቀም !

የተፈጥሮ የባህር በሮቿ ተዘግተዋል። የቆዳ ስፋቷ ተጨራምቷል። የረሀብ ፤ የቸነፈር፤ የእስራትና ግድያ ፤ የዕልቂትና የስደት ዘመን ሆኗል ። ለምልዐተ- ሕዝቡ ዓመተ-ፍዳ፤ ዘመነ መርገም ሆኖበታል ። ይህ ዘመን፤ ለአጥፊዎቿ ሀሴትን፤ ለዜጎቿ መከራንና ስቃይን አምጥቷል ። " የጨነቀው በአባቱ መቃብር ያፍራል " እንደሚባለው፤ ኢትዮጵያን የጠሉና በኢትዮጵያዊነታቸው ያፈሩ ሁሉ ከድተዋታል ። ታዲያ ዓለምና ዘመን በኢትዮጵያ ላይ ፊታቸውን አዙረውባታል ቢባል ምን ያስገርማል ? " ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ፡፤ ባለዕዳ ይቀበለዋል " ብሎ ማሰብስ እንዴት ይቻላል ?

" አይጣል ይሏል እንጅ የእሳትን መከራ ፤
ቤተክርስቲያን ያቃጥላል እንኳን የሰው ገላ ። " እንዲሉ፤

ዘመንና ዓለም ተባብረው ፊቷን የዞሩባት ሀገር፤ የራሷ ልጆች ከከዷት፤ ታዲያ ማን ሊደርስላት ይችላል ? በአደጋ ላይ የወደቀው ህልውናውን ለማትረፍ ፤ የትኛው ኃይል ነው ሊታደጋት የተዘጋጀው ? ሆነም - ቀረ ፤ ይህንን ጥያቄ በአግባቡ መመልስ ያለበት የአንድነት ኃይሉ መሆን እንደሚገባው ፤ ኢትዮጵያ መዳን አለባት የሚለው ዜጋ ሁሉ ጓጉቶ ይጠብቃል ። " ፖለቲካ ማለት፤ መሆን የሚችለውን የማየት ጥበብ ነው" ። ከተባለ፤ የአንድነት ኃይሉ ማን ነው? ለመሆኑ ይህ ኃይል አሁን በብቃት ተሰባስቦ ይገኛል ወይ ? ከሌለስ እንዴት ይፈጣራል ? ማንስ ይፈጥረዋል ? እነኝህንና ሌላች ተመሳሳይ ጥያቄዎች ከመመለሳቸው በፊት ግን ፤አንድ ሌላ አጣዳፊና ወሳኝ ጥያቄ መልስ ሊያገኝ ይገባዋል ። የዚህ ጥያቄ ምላሽ ካልተገኘ ፤ እውነተኛ ኅብረት ይፈጠራል ማለት ዘበት ነው ።

ይኸውም፤ የአንድነት ኃይል ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚቆጠረው ሁሉ፤ሊስማማበት በሚችለው መሠረታዊ - ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ተቀራርቦ ለመነጋገር ችሏል ወይ ? ይህ መሠርታዊ ጉዳይ ደግሞ፤ የሀገሪቱ ኅልውና ጥያቄ ነው ። ኢትዮጵያ እንደ ሀገር መቀጠል አለባት የሚለው ጉዳይ አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱን አለመገንዘብ፤ ወቅታዊውን የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በቅጡ አለመረዳት ይሆናል ። የአንድነት ኃይል ነው ተብሎ የሚገመተው ሁሉ፤ በኢትዮጵያ ኅልውና ላይ ቁርጠኛ ውሳኔ አድርጎ ከአንድ ስምምነት ላይ ካልደረሰ፤ ሀገሪቱን ማዳን ቀርቶ እራሱንም በህይወት ለማቆየት የሚችል አይሆንም። በመሆኑም፤ ከማንምና ከማንኛውም በላይ ይህ ጥያቄ የማያወላውል መልስና ውሳኔ ሊያገኝ ይገባዋል ።

እስካሁን ድረስ፤ ሁሉም በየፊናው - በተናጠል የየግሉን መግለጫና አቤቱታ ከማቅረብ የዘለለ፤ ፋይዳ ያለው የጋራ ተግባር ሲፈጽም አይታይም ። ለአለፉት አምሳ/ 50 ዓመታት ፤ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ምኅዳር የታየው እንቅስቃሴ፤ ሕዝብ ለመብቱ እንዲታገል ከማድረግ አንጻር ጎላ ያለ አስተዋጽኦ ያደረገ ቢሆንም፤ ግብዓት አግኝቶ የግስጋሴ ርምጃ ማሳየት አልቻለም ቢባል እንደ ተስፋ አስቆርጭ ሊቆጠር አይገባውም ። የኢትዮጵያ ሕዝብ የተሻለ አስተዳደር ለማግኘት አይከፍሉ መሥዋዕት ከፍሏል። ዐርበኛና ጀግኖች ልጆቹን አጥቷል። በዚህም አንጀቱ አርሮና ለጊዜው አንገቱን ደፍቶ ለመኖር ቢገደድም የሚከፈለውን መሥዋዕት ሁሉ ክፍሎ ውጤትን ለማየት ይፈልጋል ! ያንን የሚጠበቅ ውጤት ለማስመዝገብ ግን፤ በግድ የኅብረት ትግል እንደሚያስፈልግ ከልብ ይገነዘባል ! ወያኔም፤ ኅብረት እንዳይፈጠር የታቸለውን ሁሉ  ያደርጋል ። የተቃዋሚውን ተሸከርካሪ ባሌስትራ ይስብራል። ተቃዋሚውም በበኩሉ በየጊዜው የሚተነፍስበትን ጎማ ሳልዳሬ በማድረግ እየተጠራሞተ ይገኛል ።

እንደ ኢትዮጵያ ውስብስብ ችግሮች ያሉባትን ሀገር ህልውናዋን ለመጠበቅ ካስፈለገ፤ የጋራ ጥምረት፤ የእርስ በእርስ ትብብርና የዕምነት ትስስር ወሳኝ መሆኑን አምኖ መቀበል ያስፈልጋል ። በራስ አቅምና ብቃት ላይ የተመሰረተ ትግል ማካሄድ የሚቻለውም፤ በጋራ ዓላማ ላይ የተመሰረተ የኅብረት ትግል ሲያካሂዱ ብቻ ነው። ኅብረት-ኅብረት ስለተባለ ብቻ ኅብረት በራሱ ፈቃድ እንደማይመጣ፤ ያለፈው ተመክሮ በገሃድ አስመዝግቧል ። ህብረትን ለመፍጠር፤ ሁሉም ተቃዋሚ ኅይል ወያኔ ብሄራዊ ጠላት መሆኑን ከልብ አምኖበት፤ አስፈላጊውን መሥዋዕት ለመክፈል ቆርጦ መነሳት አለበት። ከለበጣና ከይስሙላ በላይ በተጨባጭ ተግባር ላይ ካልተሰማሩ፤ ሕብረት ሊመጣ አይችልም።

ይህ ሃቅ እንዳለ ሆኖ ግን ወያኔ አራት ኪሎ ከመሸገ በኋላ ፤ ልዩ ልዩ ተቃዋሚ ድርጅቶች፤ ኅብረት ፈጥረው ለመታገል ሙከራ አላደረጉም ማለት አይቻልም። ለታሪክ ግንዛቤና ለወደፊቱም ማጠያቂያ ሊሆን የሚችል ከሆነ፤ ዋና ዋና ሙከራዎቹን መጥቅሱ አግባብነት ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል ። እነርሱን እንዳመጣጣቸው በቅደም፣-ተከተል እንመዘግባለን ።

# ነጻ ሀሳብ

**1ኛ.** ወያኔ ገና ወደ አዲስ አበባ ከመግባቱና የደርግ ቁንጮ የነበረው፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለአደጋ አጋልጦ ከመፈርጠጡ በፊት ፤ በሀገሪቱ ላይ ያንዣበበውን አደጋ የተገነዘቡ አምስት ድርጅቶችና ሀገር ወዳድ ዜጎች ተሰባስበው፤ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅትን ( ኢዴኃቅ ) መሰረቱ።

**2ኛ.** ፓሪስ አንድና ፓሪስ ሁለት የተሰኙ ሁለት የኅብረት ሙከራዎች ተደረጉ።

3ኛ. የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ኅብረት ( ኢተፖድኅ ) ተብሎ፤ ሌላ የኅበረት ጥረት ተሞከረ ።

**4ኛ** . የአማራጭ ኃይሎች የሚል ስያሜ የተሰጠው በአዲስ አበባ ግዮን ሆቴል ስብሰባ ተደርጎ ኅብረት ፈጥሮ ተነሳ ተባለ ።

**5ኛ.** በመጨረሻ ደግሞ ፤ ከሁሉም በላይ ፤ ብዙ ታስቦበትና ሁለት ዓመት የፈጀ ከፍተኛ ርብርቦሾ ፤ ገንዘብንና ዕውቀትን የጠየቀ ሥራ ተሰርቶ፤ አስራ ስድስት ( 16) የፖለቲካ ድርጅቶችን ያካተተ ፤ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ( ኢዴኃኅ ) ተመስርቶ በመልካምና ብሩኅ ተስፋ ተግባሩን ቀጠለ። ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን፤ ለሕዝብ ከፍተኛ ተስፋና መነሳሳት አምጥቶቷል። የማይናቅም ውጤትን አስምዝግቦ እንደነበር የሚካድ አይደለም። ቢያንስ ተቃዋሚዉ ኃይል ከተደራጀ፤ አርዕድ- አንቀጥቅጥ ኅይል ሊሆን እንደሚችል በተጨባጭ አሳይቷል።

ከላይ እንዳመጣጣቸው በጊዜ ቀመር ቅደም- ተከተል የተፈጠሩት የኅብረት ድርጅቶች፤ በወቅቱ ለተነሱት ሕዝባዊ ጥያቄዎች፤ ከሞላ ጎደል ፤ ምላሽ ለመስጠት ጥረት ቢያደርጉም፤ ከስትራተጂያዊ ራዕይ አኳያ ግን፤ የሀገሪቱን ዘላቂ መፍተሄ ለማስግኘት አልታሳካላቸውም ። ከነዚህ መካከል ፤ አንዳንዶቹ፤ እንዲያውም ከናካቴው፤ ስምምነቱ የተጻፈባቸው ቀለሞች ገና ሳይደርቁ የውሃ ሽታ እየሆኑ ቀርተዋል። ጥቂቶች ደግሞ የተሰጣቸውን የሃላፊነት ቦታ እንኳን በቅጡ ማስረከብ ይቅርና እንዲያውም ስሙን ቀምተው የወያኔ ፓርላማ ወንበር ለመያዝ ተጠቀሙበት። እንዲሁም ሌሎች ብዙ ተመሳሳይ ጉዳዮችን ማንሳት ይቻል ነበር፣ ሆኖም ግን ይህ ለምን ሆነ ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ፤ የዚህ ሐተታ ዓላማ ስለአይደለ፤ ለታሪክ ተከታታዮች እንተወዋለን ።

በእኛ ዕምነት ፤ በአሁኑ ወቅት ፤ ጠንካራ የተቃዋሚዎች ኅብረት ለመፍጠር፤ በመጀመሪያ የጋራ ብሔራዊ ራዕይ መኖር አለበት እንላለን ። ቀጥሎም ሰፊው ትብብር በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ላይ የማያወላዳ አቋም ሊኖረው ይገባል። እስካሁን ይህ ባለመኖሩ፤ ጠንካራ የተቃዋሚ ኃይል ኅብረት ለመፈጠር ሳይቻል ቀርቷል ። ይህ የጋራ ራዕይ ማለት፤ የሀገሪቱን ኅልውና በመጠበቅ ዙሪያ ሊያሰባስብ የሚችል ብሔራዊ አጀንዳን የያዘ ዓላማ ያለው እምቅ ኅይል ማለት ነው። ኢትዮጵያን ከጥፋት ለማዳን የሚችል ዕምቅ ኅይል እንዳለ የማይካድ ቢሆንም፤ እምቅን ኅይል ወደ ተንቀሳቃሽ ኅይል መለወጥ መቻል አለብን ነው ዋናው ቁም ነገር። ለዕምቅ ሀብትማ፤ ከኢትዮጵያ የበለጠ ማን ሀብታም አገር ይኖራል ? የሀገራችን ሁለንተናዊ ዕምቅ ሀብት ፤ማለትም፤ የሰውና የተፈጥሮ ኅብት ተደምሮ ተጠቃልሎ ወደ ተንቅሳቃሽ ኅይል ከተለወጠና ሥርዓት ባለው ሁኔታም መጠቀም ከተቻለ፤ የፖለቲካውም ሆነ፤ የኢኮኖሚው ችግራችን ይፈታልናል የሚል ብሩኅ ተስፋ አንግበን ካልታገልን፤ አድሮ ጥጃ ከመሆን አናልፍም ።

በጋራ አጅንዳ ላይ የተገነባ ኅብረት ፈጥሮ፤ ሀገሪቱ ከገባችበት ማጥ ለማውጣት የህብረት ትግል አስፈላጊ መሆኑ በዕርግጥ ሁሉ ካመነበት፤ የሚከተሉት አምስት ጉዳዮቹን መሠረት ማድረግ ያስፈልጋል ።

**1ኛ**. ማነኛው ድርጅት/ ስብስብ ወደ ኅብረት ጉባዔው ለመሄድ ሲሰናዳ፤ የስብሰባው ቅደመ- አጀንዳ ፤ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም ማዕከል ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት ።

2ኛ. ይህ ማለት፤ የኢትዮጵያ ኅልውና፤ የግዛቷ ልዕልና፤ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የዜጎቿ አንድነትና ነፃነት፤ እንዲሁም የዴሞክራሲ ሥርዓት ማለት ይሆናል ።

**3ኛ**. በተራ ቁጥር አንድና ሁለት የሰፈሩትን መሠረታዊ ዕምነቶች አምኖ መቀበል የመጀመሪያው ርምጃ ብቻ ሳይሆን፤ ለድረድርም የሚቀርብ አይሆንም ። ይህ ደግሞ የእኛ አልፋ-ያሜጋ ብቻ ሳይሆን፤ የማንነታችን መግለጫና መርኋችን ሆኖ ቆይቷል ። ወደፊትም ይኖራል ።

**4ኛ**. ድርጅትን ድርጅት የሚያስብሉ፤ መስፈርቶችን አሟልቶ መገኘት፤ለኅብረት ኅልውና መሠረት ነው። በዘለቄታውም ፤ በአብሮነት ያገለግላል። በጉባዔ ለመገኘት ብቻ ሲባል ወይንም እኔስ ለምን ተለይቼ እቀራለሁ ከሚል እሳቤ ብቻ በጉባዔ ላይ መገኘት፤ ድርጅታዊ ህልውና በሌለበት ለስም ብቻ ገብቶ መኮፈሱም ፋይዳ አያመጣም ። እስካሁንም እንደታየው ምንም ያስገኘው እርባና አልነበረውም ። ትብብሩ (ኅብረቱ) ለትግል ቆርጠው የተነሱ ድርጅቶችን መያዙ ወሳኝ ስለሚሆን መሠረቱ በሀገር ውስጥ መሆኑ ሚዛኑን ከፍ ያደርገዋል።

**5ኛ**. የጋራ ብሄራዊ ራዕይ ያለው የጋራ ኅብረት መፍጠር፤ ቢያንስ ሦስት ዐበይት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ከገጽ 6 የዞረ

**ሀ.** ያለተቋረጠና ያልተቆጠበ ሕዝባዊ ዕምነትና ድጋፍ ይኖረዋል ።

**ለ.** ለአምባገነን ገዥዎች ሰልባ ከመሆን ራሱን ያድናል ። በራስ ኃይል ይተማመናል ። በራሱ የሚተማመን ደግሞ የሕዝብ ከበሬታና ድጋፍ ያገኛል ። ተአማኒነትንም ያተርፋል ፡፡ የሕዝብና የሀገር መከታ ይሆናል ።

**ሐ** . በራስ ኀይል ተማምኖ፤ የሕዝብንም ሁለንተናዊ ድጋፍ አግኝቶ ስለሚታገል፤ የአምባገነኖችን ዕድሜ ባጭሩ ይቀጫል ። ይህንን ዘረኛና ዘራፊ የገዥ ቡድን ፤ ከነሥርዓቱ ከስረ- መሠረቱ ፈነቃቅሎ ለማስወገድ ሲባል ፤ ለአለፉት ዓመታት የተደረገውን ጥረት በሚገባ መርምሮ፤ በአዲስ ስልትና ፈርጀ-ብዙ የኅብረት ትግል ማካሄድ የወቅቱ ወሳኝ ጥያቄ ሆኗል ። ወደ ፊትም ኅብረቱ ካልተመሰረተ፤ ሕዝባዊና ወቅታዊ ጥያቄ እንደሆነ ይቆያል ።

ይህን ሕዝባዊ ጥያቄ ለመመልስ፤ የሚቻለው ደግሞ፤ የጋራ ብሄራዊ ራዕይ ያለው ኃይል ሲፈጠር ብቻ ነው። ቅድሚያ ለብሄሬ እንጅ " ኢትዮጵያ ለእኛ ሁለተኛ ደረጃ ነች ከሚሉና አልፎም ስሟን መጥራት ዳገት ከሆነባቸው ፅንፈኞች" ጋር ኅብረት መፍጠር አስቸጋሪ ሆኖ መቆየቱ ብቻ ሳይሆን ወደፊትም የአሸዋ ላይ ግንብ ከመሆን አያልፍም ። አሁንም ሁኔታው አልተለወጠም ። የወያኔ ሰለባ የሆኑ ሁሉ፤ ሊያስቡበት የሚገባው፤ ከሁሉ በፊት የመጀመሪያው ዒላማ ፤የሁሉም የጋራ ጠላት በሆነው አገዛዝ ላይ መሆን አለበት። ይህ ደግሞ፤ ለማንኛውም ብሩኅ አዕምሮ ላለው ሁሉ የሚሰወር አይደለም ። ለሁሉም የጋራ የሆነችውን ሀገር በጋራ ከጥፋት አድኖ፤ ሁሉም የሀገሪቱ ዜጋ ፤ በጋራ ተጠቃሚ በሚሆንባት ሀገር ላይ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መስርቶ አብሮ ከመኖር የበለጠ ሌላ አማራጭ እንደሌለ የማይናውጥና ዘመን የማይሽረው አቋማችን መሆኑን ሁሉም ሊያውቀው ይገባል ። ወገናችን የሆነው ብዙሃኑ የትግራይ ሕዝብም በዚህ እንደሚስማማ አንጠራጠርም ። ይህ የፖለቲካ ሀቅ ግን ወያኔን ሲያስጨንቀው ኖሯል ። ወደፊት መሆኑ አይቀርም ብሎ ስለሚያስብ ፤ ሁልጊዜ እያባነነው፤ እንቅልፍ-አልባ እንደሆነ ይቆያል ።

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባልቆረጠው ዱላ እየተመታ፤ ባልሰየመው ዳኛ እየተረታ፤ባልመረጠው " መንግሥት " እየተፈታ የቁም-ስቃዩን እየከፈለ ይገኛል ። ሀገራችንንም ዓለምና ዘመንም ረስተውታል ። ከስቃይ ያወጡኛል የሚላቸው ኃሎችም አልተባበሩለትም። ከቀዳሚው ትውልድ ያገኘው ህልውናም ጥያቄ ውስጥ ገብቶበታል። የወረሰውን ኢትዮጵያዊነትም ለሚቀጥለው ትውልድ ለማውረስ ከሚችልበት ደረጃ ላይ አይደለም። ወጣቱ ትውልድም የሚወርሰውን ፤ የሚያወርሰው እያጣ ነው ። ከአባቱ ያልወረሰውን ደግሞ ከአያቱ መውረስ ይቸግረዋል ። በዚህ ምክንያት፡

" የባት ዕዳ ለልጅ ይባል ነበር ዱሮ፤
ባያት እዳ ገባሁ እኔማ ዘንድሮ ። " እያለ
ይማልላል!

ከገጽ 3 የዞረ

- የዩጋንዳው ሙሴቬኑ ምርጫን አጭበርብሮ እንደገና ተመርጧል። እስካሁን ከ 30 ዓመት በስልጣን መቆየቱና በሙስና መዋጡ ሳይረሳ ።

- በባዕድ ሀገር--በተለይም በአሜሪካና አውሮጳ- የተደበቁ የቀይ ሽብር ወንጀለኞች አንገት ደፍተው በመኖር ፈንታ ይባስ ብለው በኢሕአፓ ላይ የከፈቱትን ጸያፍ ዘመቻ አስመልክቶ በነዚህ ወንጀለኞች ላይ ባለው ሰነድ አማካኝነት እያጋለጡ መከሰስ አስፈላጊ እርምጃ ነው መባሉም ተነግሯል። ሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋ በዚሁ ዘመቻ እንዲሰማራም ጥሪ ተላልፏል ።የወያኔ ውጥረት ዘላቂና ለውጥ አዋላጅ እንዲሂን ህዝብ በኢትዮጵያውዊንት መሰረት እንዲያብር የተደረገው ጥሪ በዚያው ልክ ሕዝብን በጥላቻ ሊያባሉና በዚህም ወደዱ ጠሉ ወያኔን ሊጠቅሙ የሚከጅሉትንም ማግለልን ይጠይቃል ተብሏል ።

ልብ እንበለው ።
በትግላችን ኢትዮጵያን እንታደጋት !

ከገጽ 2 የዞረ

ሆኜ ብሆንማ....

በቀይ ደም ሳይሆን፣ በፋብሪካ ቀለም ቃላትን ሸላልሞ፣
ፍፁም አልነበረም፣ በባዶ ጭንቅላት፣
ሊያስነርት አታሞ !
ደሙ መሬት ፈሶ፣ አጥንቱን ከስክሶ፣
የከተበው ታሪክ፣ አፈሩን አጣቅሶ፣
ዋቢነት ያቆመው፣ የሃቅ ምሰሶ፣
የሚያስነብበው ዝክር፣ ምስክርነቱ፣
ታግሎ መሞቱን ነው፣ ለኢትዮጵያዊነቱ !
በፈፋ በሜዳ፣ ያረፈው ሠማዕቱ !
አዎ ! ትንታጎቹን ፀሀፍት፣ ሆኜ በሆነማ !
የሠማዕታቱን ገድል፣ ዘክሬ እማሰማ !
ለመጣ አፋኝ ሁሉ፣ የወጥ ቀማሽ ቅምጥ፣
አመጽ ማዳፈኛ፣ የመርገጫ ሸበጥ፣
የወንበሩ ሽፋን፣ የግማቱ ሽርጥ፣
የህዝብ አመፅ ገፍቶ፣ ዠማው ሲያዝ በምጥ፣
ወረ-ግቡ ሲሆን፣ እምቢታው ለለውጥ፣
ለፍሬ እንዳይበቃ፣ መደብደቢያ ቆመጥ፣
ከመጣው ገዢ ጋር፣ አንሶላ እሚጋለጥ፣
ቴዎድሮስ፣ ምኒልክን፣
ያገር አድባሮችን፣
እንደ ግንደ ቆርቁር፣
ባደባባይ ግጦ !
በአርበኞች ገድል ላይ፣ ሲሳለቅ አላግጦ !
ጀግና እየተባለ፣ ዛሬ ላይ የግልብጥ !
መች ይቻለው ነበር፣ ሊያጠፋ እየበላ፣ ታሪክን
እንደ ምስጥ !
የህንዶች ሃይማኖት፣ ሃቅ ሆኖ ቢሰራ፣
ዳግመኛ ሰው ብሆን፣ በዳግም ፈጠራ፣
አፈናን እምቢ እሚል፣ ፍፁም እማይፈራ!
ለህዝባዊ ትግል፣ ነዶ የሚያበራ፣
በጨለማው ሌሊት፣ መንገድ የሚመራ፣
ነበር በሆንኩ ሃይሉን፣ እሳተ-ገሞራ !

# መርገምት ህልዉ ያግኝ !

(በህያዉ ቃል)

አምናና ካቻምና፤ ልጅ በእናት ምርቃት ግንባሯን ተስማ፣
በ'ንባ ተሞሽራ፤ ለግርድና እንጀራ፣
ለአመንዝራ ዐረብ፣ የትርፍ ጊዜ ሢሳይ፣ ባልጋ ልትሞላ፣
ስትርቅ ወዳጅ ዘመድ፤ እህትና ወንድም፣ መንደር አገር ጥላ፣
ዉርደት ሞታችንን፣ በልባችን ገድለን፣
በዘበት ሸኘናት፣ ወኔያችንን ሸንተን፤
ዘራፍ አያዉቅ አባት፤ እማይመከት ጋሻ፣ ቡቡዎች ወንድ ሆነን፣
የእንባችንን ወራጅ፣ በጣቶች ፈንጥቀን፣
ወደ ላይ አንጋጥጠን - ከመለኮት መንበር፤ ከሰማይ ረጨነዉ፣
ገብረመንፈስ ቅዱስ፣ የአቡዬን ጉንጮች፣ ጨዉ'ህ ደፈቅነዉ፣
በአርዕድ- ነጎድጓድ፤ በመብረቅ ፍላፃ፣ እሳት ጅራፋቸዉ፣
የኢትዮጵያን ጠላቶች፣ ስለኛ ተፋልመዉ፣ ቡን እንዲያደርጓቸዉ፤
ይኼዉ ስንት ዓመቱ ፤ ጥልማሞት ወያኔ፣ ፍርንባዉ ሰባ እንጂ፥
እንደዉቅጥ ሙከት፣ አለተለተ 'ንጂ!
ያ የቅቤ ቅል ወዙ፤ ከቶ አልገረጣበት፣ አጀቡ አልጎደለ!
እንባችን ደማችን፣ መፍሰሱስ መች ቆመ፣ ቦይ እየነደለ!?
አለን እየሞትን - አለ እየገደለ!
ባንተዉ መጀን ኃይሉ - የቅኔዉ አለቃ፣
በገሞራህ ነዲድ፣ በቋያህ ነበልባል፤
በፍህም ረመጥህ ነዉ፤ ገና በማለዳዉ ዐይናችን የበራ፤ ነፍሳችን የነቃ፣
እናም ከዉብ ቋንቋህ፣ ለትዉልዶች ኪዳን፣
በምንባቡ ለዛ፣ ከምናብህ ጠሊቅ፣ ከፈለቀዉ ጸበል፣
ለመጻዒዉ ዓለም፣ ካስቀረኸዉ ራዕይ፣ ሳይጎድል ጠብታ፣ ሳያጥር አንድ ቃል፣
የቸርከን በረከት፣ የፍትሕ የአርነት፣ እንዲያዘንብ ሲሣይ፣
መርገምት ህልዉ ይሁን፣ በጎልዮ በግብር፣ ይዉጣ ካደባባይ።
አዎን! ወግ ይድረሰዉ! መርገምት ዕዉን ይዉረድ! በሕዝብ አመጽ ቁጣ!
ትንቀጥቀጥ ምድሪቷ!
የነጣዉ እስኪጠቁር -ጥቁሩ እስከሚነጣ!
የወያኔ እብሪት፣ የዘረኞች ትዕቢት፣ ካቡ እስከሚደረመስ፣ የቆሙባት ሰምጣ !
እንደ ሕዝቡ ልጆች፣ ደግሞ እንደ ኢሕአፓ፣
መድኅን ለኢትዮጵያ፣
አገር ሻጭ ወያኔ ! ሆዳም 'ሚከስልበት !
ኑ እሳት እንስበቅ !
ለመጪዉ ጅማሬ፣ ለነባሩ ማብቂያ !
ኑ እናንድድ እሳት !
የሕዝብ አመጽ ሰደድ፣ የሕዝብ አመጽ ቋያ፤
እንወድዳለን ተኳሽ፣ ባመጽ ወጥቶ አዳሪ፣ ባለሃሞት ጀግና !
የበረሀ ጠሮ፣ ግፍ በደል ጠራርጎ፣ እንባን የሚያደርቅ፣ ባንዳን የሚከላ !
የቀትር ላይ መብረቅ፣ ክንዱ ያምላክ ቁጣ !
ትምክህትን ደፍቆ ! ክህደት እሚያሳጣ !
አይለመጥ ጽናት፣ አይቸለስ ወኔ፣ ዝንተ-ዓለም ያልታዬ !
ወንድ እንደጺጋዬ፣ ደፋር እንደ ጋይም፣ መሪ እንደ ተስፋዬ !
እንደ ኮከቦቹ፤ ደምቀዉ እንዳፈኩት፣ የኢትዮጵያን ካስማ !
መምህር በላይነህ፣ መህንዲሱ ዑስማን፣ ያ ግርማቸዉ ለማ !
ደግሞም ከሴት ጓዶች - እንደ ዳሮ ነጋሽ ፤እንደ አበራሽ በርታ !
እንደ ቆንጂት ተክሉ ፤ ደግሞ እንደ መዝገብነሽ እንደገነት ግርማ !
ይወለዱ ልጆች !
ይፈጠሩ ጀግኖች፤ እንደ ኢሕአወሊ-ሕዝቡን ያበለጡ !
እንደ ቲቶ ጎሩይ ከነወንድሞቹ !
እንደነ ጺጋ'ምላክ* -እንደ ሙሉጌታ** ፤ ገና ከጠዋቱ ለሕዝብ የተሰጡ !
ከደማቸዉ ጠቅሰዉ፣ በሞት ጣዕር ሥቃይ፣ ታሪክ ያቀለሙ !
ለኢትዮጵያ ትንሣዔ፣ በህይወታቸዉ ምትክ፣ ክብርን የሸለሙ !
በኢሕአሠ ዓርማ ሥር፣ ታጥቀው ሲታገሉ፤
በወደቁት አምሳል፣ በየጉራንጉሩ ከገጠር ከተማ፣
ችግኞች እናጽድቅ፣ ደማቅ ዉብ አበባ፣
ኃይሉ ቃልህ ይስመር፣
ጠጣሩ እንዲላላ፣ የላላን ወጥረን !
ለአዲስ ዓለም ጅምር፣ አዲስ ጀግና እንፍጠር።

**ማስታወሻ ፡ ህዳር መግቢያዉ ላይ ፪፻፫ ጺጋ አምላክ*፤ አዋሳ ላይ ከወንድሙ ይኩኖ አምላክ ጋር የተሰዋ ኮማንደር/ ኮሚሣር፤ ሙሉጌታ ማሞ** ፤ ምኔም የማይረሳ ጽኑዕ ታጋይ፤ አዋሳ ላይ ተሰቃይቶ የተገደለ የለኩ ልጅ ፤ ቃሉ የሚረታ**

## ብሆንማ ኖሮ መሆን አቃተ እንጂ

*ሐማ ቱማ*

ብሆንማ ኖሮ፣ የዚያች ጸሐይ ጌታ፣
ጨረቃን ማወጣ፣ ጠዋትና ማታ፣
ብሆንማ ኖሮ፣ ነቢይ ተከባሪ፣
ቃሉ ጠብ የማትል በሁሉ ተሰሚ
ብሆንማ ኖሮ፣ የዚያ ትውልድ ቁራጭ፣
የዚያ የተስፋዬ፣ የዳር የአበራሽ፣
የማርቆስ፣ ይትባረክ የሁሉ ደመላሽ፣
ከወኔው ጽናቱ፣ ቢያንስ እንኳን ተቃራጭ፣
ብሆንማ ኖሮ፣ ዲያብሎስ ለሕዝብ ጠላት፣
ለሕዝብ ግን አጋሩ፣ አለኝታና ኩራት፣
ብሆንማ ኖሮ ለየባንዳው ኮሶ፣
እሬትና እንቆቆ፣
ለወያኔም ምንጩ፣ ለየቀኑ ለቅሶ፣
የማይለቅ ማነቆ፣
ጨካኝና ደምሳሽ፣ ዘረኛን ማርከሻ፣
አውደልዳይ ምሁሩን፣ መድረክ የማሳጣ፣
የገንጣዩን መንጋ፣ ማመክን የማጠፋ፣
ብሆንማ ኖሮ፣ አልሆን አልኩኝ እንጂ፣
አስቸገረኝ እንጂ፣
ህሊናዩ ሲደክም፣ ሆዴ እያበጠ፣
ከርስ አምላኩ አርጎ፣ አዋረደኝ እንጂ፣
ባለጌ ዘረኛ፣ ጠባብ ትምክህተኛ፣
ታጋይ ብሎ አቃፊ፣ ግሙን ሽብርተኛ፣
አጋር ብሎ አቃፊ፣ ውድቁን ሻዕቢያ፣
ብሆንማ ኖሮ፣ ንቁ እንደዚያ ትውልድ፣
ጽኑ ኢትዮጵያዊ፣ ሀገሩን የሚወድ፣
ነገረ ሁኔታው፣ በሆነማ ሌላ፣
ወጣቱን ማስተኛት፣ በከሸፈ ሴራ፣
የማውግዘው ሁኜ፣ ማልሰማው ቢጣራ፣
ብሆንማ ኖሮ፣ ለወያኔው ፍየል፣ የነብር ቀበኛ፣
የራበው ጅብ መንጋ፣ ለፈሪ አህያ፣
ብሆንማ ኖሮ!
መሆን አልሆን ብሎ፣ ባይቸግር ባይጎዳ፣
ሆድ አደር ባይበዛ፣ ማፈሪያ ያ ባንዳ፣
ዛሬ ቢኖርማ፣ የአርበኛው ትውልድ፣ የባንዳ ማርከሻ፤፣
የየካቲት ጀግኖች፣ የጨቋኞች ጠላት፣ የውድቆች መሸኛ
ባንሆንማ ኖሮ፣ "ሰው ጠፋ እንዴ?" አስባይ፣ ያለፈውን ሰራዥ፣
የድክመት ምልዕክት፣ ኩሩን ታሪክ በራዥ፣
ብንሆንማ ኖሮ፣ የዚህ ተጻራሪ፣
ፍጹም ቆራጥ ዜጋ፣ ታሪክ አስከባሪ፣
ሀገርን አፍቃሪ፣
የድፍረት ምልዕክት፣ አርአያ መስካሪ፣
ብንሆንማ ኖሮ፣ መሆን አቃተ እንጂ፣
ለወያኔ መርዙ፣ ገዳይ አሳዳጁ፣ ምህረት አልባ አጥፊ፣
ስቃይ ምሬት ሞትን፣ በቤታቸው ከታች፣
ክፉ አሸባሪ፣
ብሆንማ ኖሮ፣ የወያኔ ምጻት፤ ገሀነም እንጦርጦስ፣
ጨራሽ ካንሰር ህመም፣ ያ ቀሳፊ በሽታ፣ የሚባለውም ኤይድስ፣
መሆን ብችልማ!
ከአልጋ ባቆራኘው፣
ቆርጬ ቆራርጬ፣ ባስጎራው ባስጮኸው፣
የፍጹም ስቃይ ሞት፣ ባለቤት ባደርገው፣
ብረካ ብሞካሽ፣ ሰማዕት ተበቅዬ፣
ለእነ ደብተራውም፣ አልረሳሁም ብዬ፣
ብሆንማ ኖሮ፣ ደመላሽ ማኮራ፣


**ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ በየቀኑ ለ24 ሰዓት በሚቀጥለው የስርጭት መስመር በሳተላይት ፕሮግራሙን ያሰራጫል።**

**Channel Name:** **Finote Democracy**
**Satellite:** **Nilesat**
**Azimuth:** **7/8 deg West**
**Frequency:** **12.604 MHz**
**Polarization:** **Horizontal**
**Symbol Rate:** **27500**
**FEC :** **5/6**




Our mission is to assist our clients in achieving their legal, business and financial goals. The firm's emphasis is on personal attention and responsive service. Michael and Marcella Hadeed bring over 25 years of legal, business and family experience provides the ability and knowledge to quickly assess and identify options to recommend creative and cost-effective solutions, including negotiation, arbitration or litigation.

**Practice Areas:** **አገልግሎት መስኮች**

- Business and Commercial Law — የግዢ ና ሽያጭ ስራና የንግድ ህግ
- Criminal and Traffic Defense — የወንጀል ና የትራፊክ አደጋ ጥብቅና
- Real Estate and Leases — የመሬት ሽያጭና ግዧ፣ የቤት ኪራይ ስምምነት
- Family and Domestic Law — የቤተስብና ቤተሰብ ነክ እግ
- Courtroom Representation — በፍርድ ቤቶች ነገረ ፈጅነት
- Civil Litigation — የፍትሃ ብሄር ሙግት

*ታዋቂና ማንኛዉንም ጉዳይ በተቀላጠፈ መንገድ የሚያጽፈጽምሎት ጠበቃ ካስፈለገዎ አቶ ማይክል ሃዲድን በመደወል ያነጋግሩ።*

510 King Street, Suite 400
Alexandria, Virginia 22314
Office: (703) 962-7452 Toll Free: (844) ADEED.LAW
• Fax: (703) 962-7473







**ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ**
Email: efdpu@aol.com Mail address: P.O.Box 73337, Washington DC 20056
Telephone: 202 291 4217